# ከቀበና ማህደር

ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች ዓመታዊ መሰባሰቢያ ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ መጽሔት

ቁጥር 1 - ሰኔ 2006 ዓ.ም.          ሲልቨር ስፕሪንግ ፣ ሜሪላንድ ፣ አሜሪካ





አይበገሬው የቃኘው በኮርያ የስፖርት ክለብ



ስንት ሰው ያውቃሉ እዚህ ፎቶ ውስጥ . . . ?







# ማውጫ


ገፅ 4 የመጽሔቱ አዘጋጆች መልእክት

ገፅ 5 መግቢያ
- ቅድመ ታሪክ
- ዘመቻ - ጢኒጢ እሳት
- መሰናዶ

ገፅ 9 የቀበና አብሮ አደጎች ዓመታዊ የቤተሰብ ቀን
- የግል ማስታዎሻ

ገፅ 11 እስቲ እናስታውሳቸው
- A note to our children, to the very young

ገፅ 21 ከዚህም ከዚያም
- የቀበና ትዝታ
  - ከግጥም አምባ
- ድር ቢያብር
- የፎቶ አምድ


## ከቀበና ማህደር

ከአገር ውጪ የሚኖሩ የቀበና አብሮ አደጎች
ዓመታዊ መሰባሰቢያ ቀንን ምክንያት
በማድረግ የተዘጋጀ መጽሔት


ቁጥር 1 – ሰኔ 2006 ዓ. ም. (July 2014)

ሲልቨር ስፕሪንግ፣ ሜሪላንድ፣ አሜሪካ

የሽፋን ስዕል
አርአያ ዓለሙ

Design & Printing
www.kwikdp.com
619-206-0921 (Assaye)

Printed in U.S.A

# የመጽሔቱ አዘጋጆች መልዕክት

ይህን መጽሔት ያዘጋጅ ዘንድ የተቋቋመው ኮሚቴ የተጣለበትን አደራ ለመወጣት ብሎም ከሰው ፊት ሊቀርብ የሚችል ሥራ ለመሥራት ደፋ ቀና ሲል፣ ሲሯሯጥ፣ መረጃ ሲያሰባስብና ሲያቀናብር ከርሞ ሁሉን ነገር አጠናቆ የመጨረሻውን ኮፒ ለህትመት ከላከ በኋላ አንድ አብይ ጉዳይ እንደዘነጋ ይነገረዋል። የመጽሔቱ አዘጋጆች መልዕክት።

እርግጥ ነው፤ የአዘጋጆቹ መልዕክት ተዘንግቷል። መለስ ብለውም ጉዳዩን ተመለከቱት። ምን ዓይነት ተጨማሪ መልዕክት ነው የሚያስተላልፉት? ጠቅላላ መጽሔቱ ውስጥ የተካተተው ነገር ሁሉ እንደ ኮሚቴው መልዕክት ቢቆጠርላቸውም ወደዱ። እንዳለ ሙሉው መጽሔት ደግሞ ያዘጋጆቹ መልዕክት ተብሎ ሊቀርብ እንደማይችልም ተረዱ። መልእክታችን ብለው ሊያቀርቡት የሚያስቡት በሙሉ ፍንትው ብሎ በተለያየ የመጽሔቱ ክፍል ውስጥ ተገልጿል። ምንም አዲስ ነገር መጨመር እንደማያስፈልጋቸው ተስማሙ። መጽሔቱ ከዳር እስከዳር የነሱም መልዕክት ሆኖ አገኙት።

ግን ፣ እንጻፍ እንኳን ብንል፣ ያስፈልጋል እንኳን ብንል፣ ምን ነበር የምንለው? ቀበና ሲባል፣ ኮርያ ሠፈር ሲባል፣ ሸክላ ሜዳ ሲባል፣ ሚሽን ሰፈር ሲባል፣ ጃንሜዳ ሲባል፣ ሐኪም ሜዳ ሲባል ወይም ኖራ ሜዳ ሲባል ልቡ ወከክ የማይል፣ በትዝታ የማይነጉድ፣ ልዩ የደስታ ስሜትም የማይሰማው የቀቤ ልጅ የለም። ወደን አይደለም፤ ፈልገንም አይደለም። ከደማችንና ከስጋችን የተዋሃደ መቼም ሊወጣ ወይም ሊሰወር የማይችል ትዝታና ፍቅር ስላለን ነው ለሠፈራችን፣ ለዚያች እትብታችን ለተቀበረችበት ወይም ላደግንባት መንደራችን። ሠፈራችንን፣ ቀያችንን በጣም እንወዳለን፤ እኛም እንደዛው እንዋደዳለን። ድሮማ፣ ጥንትማ፣ እንዲህ እንደ ዛሬው በየአቅጣጫው ተበትነን፣ በየመስመራችን ተጉዘን ሳንለያይ፣ ሳንራራቅ ከጧት እስከ ማታ እንደመንትያ ተጣብቀን ነበር የምንውለውና የምናመሸው ብለን ስለሠፈራችን ፍቅር እንዳንጽፍ ይሄ በመጽሔቱ ውስጥ በደንብ ተገልጿል።

ያጋጣሚ ነገር ሆነና አብዛኛዎቻችን ከቀበና ርቀን፤ ከቀበና ተለይተን መኖሩን ከተያያዝነው ዘመናት ተቆጥረዋል። ደግሞ ይባስ ብሎ በርካታ ውድ እህት ወንድሞቻችን፣ እናት አባቶቻችንና አያት ቅድም አያቶቻችን ከዚህ ዓለም ትተውን ሄደዋል። እኛ ደግሞ በህይወት ያለነው በያለንበት ሆነን ቀበናን መናፈቃችን እርስ በርስም መፈላልጋችንን አላቆምንም። ለነገሩማ ጊዜ በረዘመ ቁጥር፣ ግንኙነት በላላ ቁጥር መረሳሳት ነበር ለወትሮው የሰው ልጅ እጣ ፋንታው። የኛ የቀቤዎች ታሪክ ግን ለየት ያለ ነው። መሠረቱ ጥንቱኑ ጠንካራ ነበርና ጊዜም ሆነ የቦታ ርቀት ለይቶ አለየንም። እንፈላለጋለን ለጉድ። ከሌላ ከማንም ጋር ልናነሳው የማንፈልገውን ያን የጥንት ትዝታ፣ ያን የጥንት ወግ የምንጋራው የቀቤ አብሮ አደግ እንፈልጋለን። አውጥተን ባንናገረው እንኳን ይህ ፍላጎታችን በውስጣችን ተቀብሮ ያምሰናል። ትልቅ የጎደለ ነገር እንዳለ ይሰማናል። ከቀቤ ልጅ ጋር፣ ከአብሮ አድግ ጋር፣ ከገበናችን ጋር ማውራት፣ መገናኘት፣ መጠያየቅ፣ አለሁልህ አለሁልሽ መባባል ያሻናል፣ ይጠማናል የሚለው ይሆን መጽሔቱ ውስጥ ያልገባው? የቀቤ ልጅ ሁሌም አብሮ አደጉን ሲሻ፣ አብሮ አደጉን ሲያስስ እንደሚኖር? ይሄ ይሆን እንዴ የጎደለው? የለም፣ የለም፣ በጭራሽ አይመስልም። ይሄ እንዴት ይዘነጋል።

ኑሮና ብልሃቱ ወደ ዕለት ተዕለት ጉዳያችን እንድናተኩር፤ አፍንጫችን ስር ያለውን ብቻ እንድናይ አስገድዶናል። መነፋፈቃችንን፣ መፈላለጋችንን አውቀን እንዳላወቀ ወደጎን ገፋ ገፋ እያደረግን እራሳችንን እየሸሸግን ከራሳችንም እየተደበቅን አስርተ ዓመታቶች አስቆጠርን። ለሁሉም ጊዜ አለው ሆነና ነገሩ፤ ገፋ ገፋ እያደረግን ወደጎን ለረዥም ጊዜ ያቆየነው ጉዳይ ከዚህ በኋላማ ወዴትም ልትገፉኝ፣ ልታቆዩኝም አትችሉም ብሎ አይኑን አፍጦ፣ ጥርሱን አግጦ ሊፈትነን ተነሣ። ጊዜው ደረሰና። እናም ቀቤዎችም መልስ መስጠት እንዳለባቸው አወቁ። ቀኑ መድረሱንም ተረዱ። ቀስ በቀስ በጊዜ ብዛት ተለያይተው ተራርቀው የቀሩትን ያህል፤ ቀስ በቀስ፣ ጊዜ ወስደው ረጋ ብለው መሰባሰብን፣ መገናኘትን፣ መጠያየቅን መረጡ። ያለብዙ ትግልና ጉትጎታም የመጀመርያውን የቤተሰብ መገናኛ፣ መሰባሰቢያ ቀን አከበሩ። በአካል ተገናኝተው፣ ፊት ለፊት ተቀምጠው ለማውጋት በቁ ብለን እንኳን እንዳንጽፍ ይሄም ተብሏል።

ህይወት እንደሆን አጭር ናት። በጣም አጭር። ልባችን እያሻው፣ ኑሮና ብልሃቱ ደግሞ ከወዲያ ወዲህ ንፋስ እንደመታው ዛፍ እያወላገደን፤ አፈር ፈጭተን፣ ጭቃ አቡክተን፣ ውሃ ተራጭተን እንደ አንድ እናት ልጆች ሆነን ተላልሰን ያደግነውን እህትና ወንድሞቻችንን እስከ መርሳት ሊያደርሰን ሲሞግተን የከረመው ይበቃዋል። አሁን ጊዜው ደርሷል። እንግዲህ የጥንት የጥዋቱን፣ የአንድ ቤተሰብነታችንን አድሰን፣ አጠናክረን መጠያየቅ፣ መገናኘት፣ መተሳሰብ እንደገና ጀምረናል። እግዚአብሔርም ይህን ቅን ሃሣብ፣ ይህን ከልብ የመነጨ ሃሣብ ይባርከዋል። የስብሰቡ ዓላማም ተራርቀን፣ ተለያይተን እንዳንቀር፣ በደስታም ሆን በመከራ አይዞህ አይዞሽ እንድንባባል፣ ለልጆቻችንም ታሪካችንን፣ እድገታችንን እንድናሳውቅ፣ እንድናስተላልፍ፣ የነሱም ታሪክ ስለሆነ እንድናስተምር፣ በዓመት አንድ ግዜም በአካል ተገናኝተን ለማውጋት፣ ለመወያየት፤ በቃ፤ ይህ ነው ዓላማው ብለን እንዳንል ይህም በትክክል ተጽፏል። ስለዚህ አሉ፤ ሁሉም ባንድ ድምፅ፤ ስለዚህ መጽሔቱ ሁሉንም ስላካተተ፣ ሁሉንም ስለዘረዘረ፣ ወደዛው መሔዱ ይመረጣል በሚለው ሃሣብ ላይ ተስማሙ አዘጋጆቹ፤ በመጨረሻ።

ከመጽሔቱ አዘጋጆች

# መግቢያ

## ቅድመ ታሪክ

ዕለቱ ረቡዕ ነው። እንደ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጣር የካቲት 27 ቀን 2005 ዓ.ም. (እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጣር ማርች 06, 2013)። በዚህ ወቅት "ዚ ሰንሻይን ስቴት" እየተባለ የሚጠራው የዮናይትድ ስቴትስ ክፍለሃገር (ፍሎሪዳ) ለወትሮው እምብዛም በቀዝቃዛ የአየር ንብረትነት አይታወቅም ነበር። ዛሬ ግን ትንሽ ገረፍ ያደርጋል። ይበርዳል በጣም፤ ይሸነቁጣል። ነፋሻማም ነው። በቁምጣና በካኒቴራ ብቻ ጉዞ የሚያደርግ የነበረ ሁሉ ጃኬት ብጤ ጣል አርጓል። ጀምበሯ እያዘቀዘቀች ቢሆንም ብርሃኗ ድምቅ እንዳለ ነው። "አቤት ውሃው ሲያምር" አለ ዛሬም እንደገና። የውሃ ነገር መቼም አይሆንለትም። ወደ ሥራ ዘወትር የሚመላለስበት መንገድ ነው። ነገር ግን ሁሌም እንደ አዲስ ያደንቀዋል ባየው ቁጥር። መጨረሻው የማይታይ ለጥና ጸጥ ያለ ጥቁር ሰማያዊ ውሃ ይታየዋል ከመንገዱ በስተቀኝ በኩል።

በሥራ የደከመ ዓዕምሮውንና ሰውነቱን ለማሳረፍ ከመቸኮሉ የተነሳ በምን አይነት ፍጥነት እንደነዳ ለራሱ እስከሚገርመው ድረስ ምኑንም ሳያውቀው ከቤቱ ደረሰ። ልክ ከቤቱ ደጃፍ ሲደርስ ግን አንድ የማያውቀው ስልክ መጣበት። ከምሽቱ 1 ሰዓት ከ 46 ደቂቃ ነው (7:46 PM)። ማነው? አለ ለራሱ፣ ይህን ቁጥር በጭራሽ አያውቀውም። ያስባል፣ ያወጣል፣ ያወርዳል። ጊዜው እየሄደ ነው። ስልኩ ማቃጨሉን አላቆመም፣ ይጮሃል። ላንሳው? አለ እንደገና ። እራሱን ነው የሚጠይቀው። ያ የፈረደበት ኮሜርሺያል ይሆናል አለ መለስ አድርጎ። አመነታ። ጥሪው አልቆመም። ለክፋም ለደጉም አለና አነሳው በመጨረሻ።



ሃሎ አለ። ከወድያ በኩል ያለውን ድምጽ እስከሚሰማ ቸኩሏል። ጤና ይስጥልኝ እገሌ ብሎ ስሙን ጠርቶ ጎርነን ባለ ድምጽ መለሰለት። በጣም ይቅርታ፣ አላወቅሁም። ማን ልበል? አለ። ደዋይ ኮራ ባለ ድምጽ አሁን እውነት ይህ ድምጽ ጠፍቶህ ነው . . . እገሌ? አለው። አሁንም ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ በጭራሽ አላወኩህም ብሎ መለሰ። ይባስ ብሎ እገሊትስ ደህና ነች? ብሎ የባለቤቱን ስም ከነአባቷ ጠርቶ ጠየቀው ደዋይ። ይሄኔ ነው መሸሽ! አለ በሆዱ። እንዴ! አንተ ማነህ? በእግዚአብሔር ንገረኝ ብሎ ተማጸነው። ደዋዩ ከት ብሎ ሳቀና . . . ጉቺ ሱራፌል እባላለሁ አለው ። ኧረ በተሰቀለው! ጉቺ ሱራፌል! ከየት ምድር ተገኘህ? ካለሁበት ነዋ። አንተማ አንድ ስቴት ነን ብዬ ስኩራራ ጥለኸኝ ሄደሃል ለካ! አለ ቀጠል አድርጎ ጉቺ፤ አይ አንተ ደግሞ። ሌላ ዘፈን እኮ መጥቷል። ካንተ ስቴት ከለቀቅኩኝ ዓመታት ተቆጠሩ እኮ አለውና ለወጉ መንደርደርያ የቀረበውን ጥያቄ መለሰ። ከዚያማ ምኑ ቅጡ ይነገራል እቤቱ እስኪደርስ ይጣደፍ የነበረው ሰው ከመኪናው እንኳን ሳይወርድ ለረጅም ጊዜ አወሩ።

ከራስ፤ ከቤተሰብና ከልጆች ደህንነት ጥያቄ በመነሳት የአሜሪካንን ኑሮ ዳሰሰ አደረጉና ሁሌም የወግ መደምደምያ ወደሆነው አገር ቤት ብሎም ቀበና ዘለቁ። የቀበናን ትዝታም በስሱ ዳሰስ አደረገው ከዚህ በኋላ እንደገና መጠፋፋት እንደማይገባቸው ተማማሉና ያንን ጣፋጭና ያልታሰበ ንግግር ቋጩ። ተሰነባበቱም።

ስልኩ በርግጥም ተዘግቷል፤ ጉቺም መስመር ላይ የለም አሁን። ሰውየው ግን ቀበና ስምጥ ብሎ ገባ። ለወትሮው እንደሚያደርገው ልብሱን ቀያይሮ ከቤተሰቡ ጋር ለራት በመቀመጥ ፋንታ፤ ፈንጠር ብሎ ለብቻው የሆነ ነገር ማውጣትና ማውረድ ተያይዟል። ይቆዝማል። እራሱንም እንዲህ ሲል ጠየቀ፣ ምን ያህል ነው ጉቺ ሰፈሩንና አብሮ አደጎቹን የሚወደውና የሚናፍቀው? ምን አይነት ልብ የሚነካ ሰላምታና ፍቅር ነው? ብሎ ጠየቀ ራሱን እንደገና። ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የሰማሁትን እኮ ነው የመሰከርኩት አለ። ከዚህ ቀደም ብዙ ሰዎች ነግረውታል። ሳሙኤል ደሬሳና ጉቺ ሱራፌል ምን ያህል የሰፈር ልጆችን እንደሚጠይቁና ለማገናኘትም እንደሚጥሩ። እንዴት አንድ ዘዴ ተፈጥሮ መሰባሰብ አልተቻለም ግን? እስከዛሬ ለመሆኑ የሞከረ ሰው ይኖር ይሆን? እያለ እራሱን በራሱ በጥያቄ ማጣደፉን ተያይዞታል። ይህን የመሰለ ጉጉትና ጥረትማ በወዲያም በወዲህም ብሎ ፍሬ ማፍራት አለበት ብሎ ለራሱ ቃል ገባ። አሁን የሆነ መሰለውና ፈገግም አለ።

ከየት ነው የሚጀመረው? አለ። እራሱን ነው የሚጠይቀው። ሲያስበው መጨረሻው የማይታይ አቀበት ሆነበት። ጸጥታ ሰፍኗል። እሱም በሃሳብ ባህር ውስጥ ጥልቅ ብሎ እየዋኘ ነው። መጠበቁ የታከታት ባለቤቱ ጠጋ አለችና እንዴ! የዛሬው ደግሞ የምን ጉድ ነው ለብቻህ አፍዝዞ የጎለተህ? አለችው። ከሰመጠበት ጥልቅ ሃሳብ እንደመባነን አለና ይገርምሻል እኮ! ብሎ ጀመረና ገጠመኙን ባጭሩ አስረዳት። መጨረሻ ላይም እንዴት ግን አንድ ነገር አይደረግም እንዲህ የሚነፋፈቁ አብሮ አደጎችን ለማገናኘት? ብሎ ጠየቃት። እሱን በኋላ እመልስልሃለሁ። አሁን ግን እየጠበቅንህ ስለሆነ ልብስህን ቀይርና እራት እንብላ አለችው።

እራቱን እንደ ነገሩ ቀማመሰና ሃሳቡን ሳይቀይር በቀጥታ ወደ

ስልኩ አመራ። መጀመርያ የደወለው ግርማ ታደሰ ጋ ነበር። ካጭር የሰላምታ ልውውጥ በኋላ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ በመግባት የምሽቱን ገጠመኝ አወጋው። በጣምም እንደተገረመ፣ ልቡም እንደተነካና ይህን እንዲህ የሚነፋፈቅና የሚፈላለግ ቤተሰብ ለማገናኘት አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት አሳሰበው። ቀጠል አድርጎም ከጥቂት ወራት በኋላ በሚደረገው በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ በዓል ላይ እንዳነጣጠረ በመጠቆም ሃሳቡን ገለጸለት። ይህን በዓል አስታከን ዋሽንግተን ዲሲ የምንሰባሰብበት ምክንያት ቢፈለግስ? ምን ይመስልሃል? ብሎም ጠየቀው።

ግርማም ዕቅዱ የተቀደሰ ነው በማለት የመጀመሪያውን ቡራኬ ከሰጠው በኋላ ሙሉ በሙሉ ሃሣቡን እንደሚደግፍም ገለጸለት። ከዚህ ቀደም የተደረጉትንም ጥረቶች በዝርዝር አስረዳው። ሃሳቡ በአብዛኛው ሰው ዓዕምሮ ውስጥ ያለ ቢሆንም ጠንክሮ ስላልተገፋበት ብቻ ነው እስካሁን ወደኋላ የተጎተተነው አለ። በአዲስ መንፈስ መቀጠል እንደሚገባም አስገንዝቦ በሁሉም ነገር ተሳታፊና ተባባሪ እንደሚሆንም አረጋገጠለት። ለሚችለው ሰው ሁሉ ስልክ እንደሚደውል ቃል ገባ።

## ዘመቻ - ጢኒጧ እሳት

ታሪከኛዋ የየካቲት 27ቷ የጉቺ ሱራፌል ስልክ የለኮሰቻት ጢኒጧ እሳት ቀስ እያለች በጥንቃቄ መቀጣጠሏን ተያያዘችው። የጉቺ ስልክ እንደ ክብሪትም ያደርጋታል። ለተቀደሰ ዓላማ ተጭራለች። አንዱ ላንዱ፣ የሰማው ላልሰማው እያቀባበለ ከደቡብ የዩናይትድ ስቴትስ ክፍላተ ሃገራት በመነሳት በራሊ ኖርዝ ካሮላይና አቋርጣ አትላንታን ጎብኝታ ቨርጂኒያን ዲሲንና ሜሪላንድን አካላ ወደ ምዕራብና ሰሜን በማምራት ኦሃዮንና ካሊፎርኒያን ተሳልማ በቺካጎ በማቋረጥ ካናዳን ከምስራቅ ወደምዕራብ አማትራ አትላንቲክን በድፍረት በማቋረጥ ለንደን ከተፍ አለች። ጢኒጧ እሳት።

ሁሉም ሃሳቡን ደገፏል። አብዛኛውም በጉዳዩ ለመግፋት ቆርጧል። እናም ሃሳባቸውን ብሎም ናፍቆታቸውን በተናጠል ሳይሆን በጋራ ለመግለጽ ወሰኑ። ቀኑም ተቆረጠ። መጋቢት 20 ቀን 2005 ዓ.ም. (ማርች 29,2013)። ያቺ ታሪከኛ ስልክ ከተንጫረረች ከ 23 ቀናት በኋላ መሆኑ ነው። የመገናኛውም መንገድ ኮንፈረስ ኮል እንዲሆን ተወሰነ።

በጉጉት ሲጠበቅ በነበረው በመጀመርያው የመጋቢት 20ው የስልክ ስብሰባ ላይ ሰለሞን ኃድጎ (ጋንፋሬ)፣ ግርማ ታደሰ፣ ሰለሞን አሰፋው፣ አጥናፉ በቀለ፣ ጉቺ ሱራፌል፣ ደረጀ ዘውዱና ገዛኸኝ ታደሰ ተገኙ። ለዘመናት ሳይገናኙ፣ ሳይተያዩ፣ አንዱ ሌላኛው የት እንዳለም ሳያውቅ፣ ይባስም ብሎ አንዱ ሌላኛው በህይወት ይኑር አይኑር እንኳን ሳይተዋወቁ ነበር በርካታ አስርተ ዓመታት የተቆጠሩት።

የሰላምታ ልውውጡ ለዛና ጥልቀት፣ የናፍቆት አገላለጹና ቃናው ምነው በመቅረጸ ድምጽ በቀረ ኖሮ የሚያስብል ነበር። አንዱ ጥያቄ ሌላውን፣ አንዱ ቀልድ የባሰውን እያነሱ እንዲሁ ተሰብሳቢው ሁሉ በደስታ እንደ ቧጀ ደቂቃዎች ብሎም ሰዓታት ነጎዱ። ደግሞ መለስ ይሉና የጥንቱን የጧቱን ጨለፍ ያደርጉና ካጠገባቸው የሌሉትን፣ ላንዴም ለወዲያኛውም የሄዱትን ብርቅየዎቹን፣ ጀግኖቹን፣ ምትክ የለሾቹን ያነሱና ይቆዝማሉ። ይተክዛሉ። እልም ብለው ይነጉዳሉ በሃሳብ። እንደገና ደግሞ ያለ የሌለ አቅማቸውን አሰባስበው፣ አንጀታቸውን ቋጠር አድርገው፤ የነምትክ የለሹን ውለታ የምንከፍለው፣ የነሱን እልህ የምንወጣው እኛ አንድ ሆነን፣ በፍቅር ተሳስረን ለቁም ነገር ስንበቃ ብቻ ነው። ያኔ ነው ሃውልታቸውን የምናቆመው ይላሉ። ይማማላሉ። ቁጥራቸው ያነሰ ይምሰል እንጂ ልባቸው፣ እምነታቸው፣ ጥንካሬያቸውና እልሃቸው የትዬለሌ ነው። ያስቀናሉ ከልብ።

ሁሉንም የቀበና ትዝታ ዛሬ አውርተው ለመጨረስ የሚቃጡ ይመስላሉ። ወደ ስፖርቱም ይገባሉ። ጤና ቡድኑን፣ ጂንሜዳን፣ አክሮባቱን፣ ሃኪም ሜዳን፣ ቡሄና እንቁጣጣሹን ሁሉን ይዳስሳሉ። በቃ ያልረገጡበት የለም። ወይ ናፍቆት፣ ወይ ትዝታ፤ እንዲህ ያደረጋል? እገሌስ እባክህ? ብሎ አንዱ ከሰላሳዎቹ ዓመታት በፊት ከቀበና የወጣው ይጠይቃል። መልሱን በጉጉት እየተጠባበቀ። አንተስ እውነትም በውሉ ከቀበና ተለይተሃል። አለው ሌላኛው። እሱንም አታውቅም እንዴ? ምን ተፈጠረ እባክህ? ብሎ በድንጋጤ ጠየቀ ከቀበናና ከቀበና ልጆች ለዘመናት ተራርቆ የሰነበተው ሰው፤ መልሱ አንደፈራው አስደንጋጭ ነበር። አንተ ስለራቅህ ነው እንጂ ብዙ ወጣት እህት ወንድሞቻችን እኮ በተለያየ ምክንያት ተለይተውናል። ቀበና እኮ የተረገመች ያህል ብዙ እንቁ ልጆቿን አጥታለች። ምን እሱ ብቻ አዛውንቱም እኮ የሉም። ያቺ የድሮዋ ቀበና፣ የድሮዋ ኮርያ ሰፈር፣ የድሮዋ ሃኪም ሜዳ፣ የድሮዋ ኖራ ሜዳ የድሮው ቀበና ወንዙ ራሱ አሁን የሉም። ትዝታቸው ብቻ በምናባችን ይንገዋለላል እንጂ።

ጎበዝ! አለ አንዱ ከመሃል፤ እንደው ሳናስበው እልም ብለን ቀበና ገብተን ቀልዱን ከቁም ነገር፣ የሚያስቀውን ከሚያሳዝነውና አንጀት ከሚበላው እያቀላቀልን ስናወጋ ሳናስበው ሰዓቱ ነጉዷል። እንግዲህ አጀንዳውን ተከትለን እንወያይ። የኛ ትዝታ፣ የቀበና ወግ ተዝቆ አያልቅም፤ እንኳንም ብቻ አምላክ አገናኘን እንጂ ቀስ እያልን እንኮመኩመዋለን አለ። በሃሳቡ ሁሉም ተስማሙና ወደ እለቱ ስብሰባ ገቡ።

ለመደበኛው ስብሰባ የተያዘው አጀንዳ የተንዛዛ አልነበረም። አንድ ጉዳይ ብቻ ነበር። እንደ ወንድምና እህት፣ እንደ አንድ ቤተሰብ ያደግንና የኖርን ሰዎች እንደ ጨው ዘር በምድር ላይ ሁሉ ተዘርተን እንገኛለን። እንዲሁ እንደ ዋዛ ከተውነው ተለያይተንና ተረሳስተን እንቀራለን። እና፣ እንደተለያየን እንዳንቀር ምን እናድርግ? ይህ ነበር አጀንዳው። ሁሉም ሰሞኑን በየግላቸው ጉዳዩን ሲያወጡና ሲያወርዱ፣ ላልሰማውም እየደወሉ ሲያስረዱ፣ እርስ በርስም እየተደዋወሉ ሲመካከሩ ስለከረሙ ጊዜ ሳያቃጥሉ ወደውሳኔ ደረሱ። የምንፈልገው መገናኘት፣ መጠያየቅ የእግዚአብሄር ፈቃድ ከተጨመረበት ደግሞ በዓመት አንድ ቀን የቤተሰብ መሰባሰብያ (family reunion) ቀን ማድረግ። ተባባሉ። ዓላማው ሁሉንም የቀበና አብሮ አደጎችን ማሰባሰብ ብቻ ይሆናል ተባባሉ። ይህን ቤተሰብ ለመቀላቀልም መስፈርቱ ይኸው ብቻ ይሆናል። የቀበና ኮርያ ሰፈር አብሮ አደግነት። ሌላ መስፈርት የለውም። አበቃ።

አንደኛው እንደገና ኀበዝ አለ። ኀበዝ፣ ይህ ስብስብ በምንም አይነት በፖለቲካ፣ በዘርና፣ በሃይማኖት ጉዳይ ዙሪያ እንደማያጠነጥን ለምናገኘውና ለምንጋብዘው ሰው ሁሉ አሰረግጠን ማስረዳት አለብን። መልዕክታችን ግልጽና ቀጥተኛ ሊሆን ይገባዋል፤ ተለያይተን እንዳንቀር መላ እንፍጠር። አበቃ፤ ይህ ነው ብቸኛ አላማው። አለ፣ ፈርጠም ባል አነጋገር። ሁሉም በሃሳቡ መስማማታቸውን ገለጹለት። እግዚአብሄር ያክብርህ አለ ሌላኛው ቀበል አድርጎ። ይህ ነው አላማው። ህይወት አጭር ናት። ተበትነን የቀረነው እረጅም ቫኬሽን ላይ ሆነን አይደለም። ከሃኪም ሜዳ የራቅነው ለሽርሽር ወጥተን አይደለም። እንደዛ አይነት ስሜት በልባችን ካለ ደግሞ በጣም፣ እጅግ በጣም ተሳስተናል። በቃ፣ የምር ነው ከቀበና ጋር የተለያየነው፣ የተራራቅነው። አብዛኛዎቻችን ተመልሰን ሐኪም ሜዳን ድጋሚ ሳንረግጥ፣ ቀበና ድጋሚ ሳንኖር ባለንበት እንደዋዛ እንሸኛለን። ወደ አይቀሬው የላይኛው ቤታችን። አይገርማችሁም ግን? አለ ቀጠል አድርጎ። መቼም ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው። ይህን ነገር ሁላችንም ስንመኘው፣ ስንፈልገው ኖረናል። ነገር ግን እግዚአብሔር የፈቀደው ቀን ይህ ሆነና አሁን ተሰባሰብን። እውነትም ለሁሉም ጊዜ አለው። አለ የልቡን አውጥቶ።

ይህ መቼም ተዓምር መሆን አለበት። ትልቅም ፀጋ ነው። መታደልም ነው። እንዴት ሁሉም አንድ ቋንቋ ያወራሉ? በእውነት ሁሉም ቀደም ብሎ ከተዘጋጀ ጽሑፍ ላይ የሚያነቡ ነው የሚመስሉት። መኖሪያቸው ግን አራንባና ቆቦ ነው። ተገናኝተው አያውቁም በአካል። ሌላው ዕድምተኛ ደግሞ መስመሩን ተቀበለና እንዲህ አለ፤ ይህን እውነታ ከተረዳን፣ ይህን ሃቅ ካመንን ከላይኛው ቤት ሽኝታችን ወዲህ አንድ ግዝፍ ቁም ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል። የታሪክም ግዴታ አለብን፤ ወደድንም ጠላንም። አባቶቻችን ጫካ መንጥረው፣ ቀበናን ቆርቁረው፣ መረዳጃ ዕድሩን፣ ጽዋውን፣ ማህበሩን አቋቁመው፤ ትምህርት ቤቶቻችንን አመቻችተው፣ መጫወቻ ቦታችንን አሳምረው ቀበናን ምቹ ስፍራ አድርገው አሳድገውናል፤ አንድ ቤተሰብ ሆነው። ከአንድ እናት፤ ከአንድ ማህፀን የተገኘን ያህል። እኛ ደግሞ በተራችን ያባቶቻችን አጽም እንዳይወቅሰን የነሱን ያህል እንኳን ባይዋጣልን፤ ያቅማችንን አንዲት ቁም ነገር ለመሥራት እንኳን መድፈር አያቅተንም። ወርቅ ላበደረ ጠጠር እንዳይሆን ነገሩ። የቀበናን ትዝታ፣ የቀበናን ታሪክ እስከ ወዲያኛው ህያው ማድረግ። ለልጆቻችን ማስተላለፍ። ከትውልድ ትውልድ እንዲሸጋገር ምክንያት መሆን። የተባረከ የተቀደሰ ተልዕኮ። በቃ ይኸው ነው፤ ብሎ የታመቀ ሃሳቡ እንኳ ባያልቅም ንግግሩን ደመደመ።

እንግዲህ በዓላማው ዙርያ ብዙ የተነጋገርንና የተስማማን መሰለኝ አለ እስካሁን ብዙም ሳይናገር በጥሞናና በተመስጦ ሲከታተል የነበረ ሰው። ውይይታችን፣ ሣሳባችንና ህልማችን ተበትኖ እንዳይቀር ሰብሰብ አድርገን ሸብ እናድርገው። እንሰረው። አለ በዛ ጎርነን ባለ ድምጹ። ሁሉም ጸጥ ብለው እያዳመጡ ነው። እንግዲህ አለ ጉሮሮውን ሞረድ አደረገና በድጋሚ፤ እንግዲህ የሁላችንም ሃሳብ በሚገርም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። የታሪክ አደራ አለብንና ህብረታችንን መልሰን፣ አንድ ቤተሰብነታችንን አድሰን፣ የቀበናን ትዝታ ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ። በነገራችን ላይ ከመሰባሰብ፣ ከመጠያየቅና በዓመት አንድ ቀን ከመገናኘት ዘልቀን በሁለት እግራችን መቆም ስንጀምር የቀበና ወገኖቻችንን የምንረዳበት እርስ በርሳችንም የምንረዳዳበትን መንገድ መተለማችን እንደማይቀር በዓዕምሯችሁ እንድትይዙ አስገነዝባለሁ አለ በአንክሮ።

ይህ የስልክ ስብሰባም በየአስራ አምስት ቀኑ እንዲደረግ ወሰኑ። የሚቀጥለውም የስልክ ስብሰባ (ኮንፍረስ ኮል) ከአስራ አምስት ቀን በኋላ መጋቢት 03 ቀን 2005 ዓ.ም. (ኤፕሪል 12, 2013) እንዲሆን ተወሰነ። እያንዳንዱ ተሰብሳቢም የተቻለውን ሁሉ ሰው ለሚቀጥለው ሰብሰባ ብሎም በሰኔ ወር ውስጥ ሊደረግ ለታሰበው ታላቅና የመጀመርያው መስራች የቤተሰብ መሰባሰቢያ (ፋሚሊ ሪዩኒየን) እንዲጋብዝና ዓላማውንም በግልጽ እንዲያስረዳ ሃላፊነት ተቀበለ። ከዚያም ስብሰባው ኦፊሽያሊ ተዘጋ።

አንዱ. . .እንደገና እሺ እባክህ? አለ ስብሰባው ኦፊሽያሊ ከተዘጋ በኋላ። ሌላኛውም መልስ ሰጠ፤ አለን! እግዚአብሔር ይመስገንና አለ።ታሪክ ሊቀጥል ነው እንደገና።ወግ ሊደራ ነው እንደገና። ስብሰባው አልቋል ምንም እንኳን የስልኩ መስመር ክፍት ቢሆንም፤ እነሱ ግን መለያየት የሚችሉ አይመስሉም። አንድ ሁለት ሦስቱ ጉዳይ ስላላቸው ተሰናብተው ወጥተዋል።

ወግ፣ ጨዋታ የፈለጉት ግን አልወጡም፤ አሁንም አሉ። እገሊትስ እባክህ? ብሎ ጠየቀ ትዝ ያለችውን የልጅነት ጓደኛውን አንስቶ፤ እሱንም አታውቅም? መላሹም ቀጠለ፤ ጠያቂ ሳያስብው ነው እንጂ ይህን ያነሳው መልሱን እንደማይወደው ልቡናው ያውቃል። አገባች እኮ የሚል መልስ መስማት አልፈለገም። አይ እድሉ! ያው ነበር መልሱ። የመቼህን ነው አግብታ የሦስት ልጆች እናት ሆናለች እኮ አለው። ጠያቂ ድምጹ ለጥቂት ደቂቃዎች ጥፍት አለች። ምነው አፌን በጠረቀመው ብሎ እራሱን ወቀሰ። ቀስ ብሎ አዘናግቶም ወጉን ተቀላቀለ እንደገና። ብቻ የባጥ የቆጡን ሲያዋሩ፤ አንዱን ሲያነሱ፣ ሌላውን ሲጥሉ ቆዩ። መቼ ጨክነው እንደተሰነባበቱ ግን እግዜር ይወቅ።

የመጀመርያውን የስልክ ስብሰባ ካደረጉ እነሆ አስራ አምስት ቀናት ተቆጥረዋል። እንዳይደርስ የለም የሁለተኛው ቀጠሮ ቀን ከች ብሏል። ኤፕሪል 12, 2013 ዓ.ም.። በመጀመርያው ስብሰባ ላይ የተሰጣቸውን አደራ አክብረው ላለፉት አስራ አምስት ቀናት ዘመቻውን ሲያጧጡፉ ነው የከረሙት። ቀና ደፋ ሲሉ። የቀቤን ልጅ ሲያስሱ። ሲጋብዙ፣ ጉዳዩንም ሲያስረዱ። አምበሶቹ። ሰዓቱ ከምሽቱ 4 ሰዓት ነው በምስራቃዊው የዩናይትድ ስቴትስ የሰዓት አቆጣጠር። ታዳሚዎችም እየደወሉ ነው። እየገቡ ነው።

## መሰናዶ

ቁጥራቸው ጨምሯል ከመጀመርያው ስብሰባ ጋር ሲወዳደር። በጉጉት ሲጠበቅ የነበረውን ሁለተኛውን ስብሰባ የተቀላቀሉት ሰለሞን አስፋው፣ ጋንፋር፣ ዳንኤል አርጋው ሙሉነህ ለገሠ፣ ደረጀ ዘውዱ፣ ወርቁ ዳመና፣ አጥናፉ በቀለ፣ አፈወርቅ መኮንን፣ ዓለሙ ለገሠና ገዛኸኝ ታደሰ ናቸው።

የሰላምታ ልውውጡ ጦፏል። የመጀመርያው ስብሰባ ላይ ያልተገኙና

ላለፉት አስርተ ዓመታት አንዱ ሌላኛው በህይወት ይኑር አይኑር እንኳን የማይተዋወቁ ነበሩ ከመካከላቸው። ልክ እንደመጀመርያው ስብሰባ ሰላምታ ልውውጡ፣ ቀልዱ፣ ትዝታውና ደግሞም ሃዘን ትካዜው በሰፊው ተይዟል። እንዲሁ ሲሳሳቁና ሲጫጫሁ ሰዓታት ነጎዱ።

በመጨረሻም ወደ ቁምነገሩ፣ ወዳሰባሰባቸው ጉዳይ መለስ አሉ የሰዓቱን መብረር ካጤኑ በኋላ። የዛሬው አጀንዳ በርከት ያለ ነው። ስብስቡን ለማጠናከርና ሌሎች አብሮ አደጎቻችንን ለማምጣት ምን መደረግ አለበት? በአካል የምንገናኝበትና መስራች ስብሰባ የምናደርገው መቼ ነው? ቦታውስ? እስከዛውስ ምን ዓይነት መሰናዶ ማድረግ ይጠበቅብናል? ይህን መሰናዶስ የሚመሩትና የሚያቀናብሩት እነማን ናቸው? ለመሰናዶው ወይም ለበዓላችን የሚያስፈልገው የገንዘብ ወጪስ? እነኚህ ነበሩ ለዕለቱ ውይይት የተያዙት ነጥቦች።

ስርዓት ባለውና ጨዋነት በተሞላበት መንገድ ለረዥም ጊዜ ሲወያዩ ቆዩ። አንዱ ሃሳብ ሲሰጥ፣ ሌላኛው ሲቃወመው፤ ደግሞ ሌላ አስተያየት ሲሰነዝር፣ ለተነሱ ጥያቄዎችም መልስ ሲፈለግ፣ አንዱ መንገድ የማያዋጣ መስሎ ሲታይ አማራጭ መንገድ ሲታሰስ ተቆየና በመጨረሻ በአካል የመገናኛውና መስራች ስብሰባ የሚደረገበት ቀን ሰኔ 25 ቀን 2005 ዓ.ም. (ጁላይ 6, 2013)፤ ቦታውም ሜሪላንድ እንዲሆን ተወሰነ። ጋንፉሬና አጥናፉ ደግሞ የዝግጅቱ መሪዎችና አስተባባሪዎች ሆነው ተመረጡ። ስብስቡን ለማጠናከርና ሌሎችንም ለመጋበዝ እያንዳንዱ በግል ኃላፊነት ከመውሰዱም ባሻገርና የሥራ ክፍፍልም ተደረገ። ወጪን በሚመለከት ደግሞ ለዝግጅቱ የሚያስፈልገውን ሁሉ በፈቃደኝነት ተከፋፍለው ለመሸፈን በደስታ ወሰኑ። የሚቀጥለውም ሦስተኛው ስብሰባ ኤፕሪል 28 ቀን 2013 ዓ.ም. እንዲሆን ተስማሙ።

በኤፕሪል 28 ቀን 2013 ዓ.ም. ስብሰባ ላይ ደግሞ ጋንፉሬ፣ አጥናፉ በቀለ፣ ዳኛቸው ወንድሙ፣ ሰለሞን አስፋው፣ ወርቁ ዳመና፣ መላኩ ይልማ፣ ግርማ ታደሰ፣ ደረጀ ዘውዱ፣ ሙሉነህ ለገሠ፣ ጉቺ ሱራፌል፣ አፈወርቅ መኮንን፣ በፍቃዱ ምንውየለትና ገዛኸኝ ታደሰ ተገኙ። ትዝታ ሚደቅሳ፣ ዝማም ዮሐንስና ዳዊት ሣህለማርያምም በነኚህ የመሰናዶ ስብሰባዎች ላይ በተለያየ ጊዜ ተሳትፈዋል። ዝግጅቱ በሚደረግበት በሲልቨር ስፕሪንግ ሜሪላድ አካባቢ የሚኖሩ አብሮአደግ የኮርያ ሰፈር እህቶቻቸውም ለግብዣው የሚሆነውን ምግብ በደስታ እንደሚያሰናዱ ቃል እንደገቡላቸው ተገለጸ። ከዚህ ዓለም በሞት የተለይዋቸውን አብሮ አደግ እህት ወንድሞቻቸውንም በዓመታዊው ሰብሰባቸው ላይ ለማሰብም ወሰኑ። በዚሁ መሠረትም የመጀመርያው የቤተሰብ መሰባሰቢያ ላይ በቀይ ሽብር ህይወታቸውን ያጡትንና የቀብር ስርዓት እንኳን ሳይደረገላቸው የተለዩትን ለማሰብ ተስማሙ። በዚህ በሦስተኛው ስብሰባም ሆነ ከዚያ በኋላ በየአስራ አምስት ቀኑ በተደረጉት ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ የስብሰባው መሪዎችና የመሰናዶው አቀነባባሪዎች የሆኑት ጋንፉሬና አጥናፉ መሰናዶውን በሚመለከት ማብራሪያ ሲሰጡ፣ የሥራ ክፍፍልም ሲያደርጉና ሌሎችንም ጉዳዮች ሲያወያዩ ከረሙ።

ይህን ቤተሰብ የተቀላቀሉት ሁሉ እንደ አንድ ሰው ሆነው፣ ተከባብረው፣ ተባብረውና ተስማምተው ዘለቁ፤ ጉዳያቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ የተጨመረበት ስለነበረም ሃሳባቸውን ለመፈጸም በቁ። ክብሩ ይስፋና።



በመጀመሪያው የቀበና ኮርያ ሠፈር የአብሮ አደጎችና የቤተሰቦቻቸው መሰባሰቢያ ቀን ላይ ከተገኙት፤ ጁላይ 6 ቀን 2013

# የቀበና አብሮ አደጎች

## ዓመታዊ የቤተሰብ ቀን



በመጀመሪያው የቀበና ኮርያ ሠፈር የአብሮ አደጎችና የቤተሰቦቻቸው መሰባሰቢያ ቀን ላይ ከተገኙት፤ ጁላይ 6 ቀን 2013

መግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው የሳሙኤል የጉቺ እና የግርማ ጥረት ፍሬ አፍርቶ፣ ሁላችንንም ቀስቅሶ የምንገናኝበትን ጊዜ ለማቅረብ ጥረት ስናደርግ ከረምን። እኔም አዳሬም ውሎዬም ቀበና ሀኪም ሜዳ ሆነ፦ በሃሳብ። የእኔነቴ  መገለጫ ቀበና፣ ያ የልጅነት ጊዜ እንደ ህልም እየሆነ ዝምታ እና ትካዜ ሆነ ስራዬ። አብሮ አደጎቼን የማግኘትና በአይን የማየት ፍላጎቴ እየጨመረ መጣ። የምንገናኝበትን ቦታና ቀን ከተወሰነ በኋላ እኛም በግላችን ዝግጅታችንን ቀጠልን። ከዋናው ፕሮግራም ከሁለት ቀን በፊት በሆቴላችን ውስጥ የመጀመሪያውን ግንኙነት እንድናደርግና እራት እንድንበላ ለኮሚቴው ጥሪ አደረግን። ያቺ ታሪካዊ ምሽት ከዋናው ግንኙነታችን በፊት እንድታለማምደን አስበን ነበር ያደረግናት።

ሰዓቱ ደርሶ የመጀመሪያው እንግዳችን ማን ይሆን እያልን በጉጉት ስንጠብቅ በር ተንኳኳ። ቀበናዎች መሆናቸውን አልተጠራጠርንም። ሁለት ጎረምሶች። ባለ አፍሮውን ወዲያው አወኩት በፍቃዱ ምንውየለት ነበር ከለንደን። ሁለተኛው ደግሞ አጥናፉ ነበር ከሜሪላንድ። አጥናፉ በቀለን በጣም ልጅ ሆኖ ነው የማውቀው። ከመቸው ፀጉርህ ተመለጠ? በመጀመሪያ የጠየኩት ጥያቄ ነበር የኔን እያሻሸሁ። የሚቀጥለው እንግዳችን ዳንኤል አርጋው ነበር ከካናዳ። ያው የዱሮው ነው ትንሽ ከመክሳቱ በስተቀር። ግርማ ታደሰ ከነልጆቹ ከቨርጂኒያ፣ ገዛኸኝ ታደሰ ከነቤተሰቦቹ  ከፍሎሪዳ፣ ሙሉነህ ለገሰ ከአትላንታ ጆርጂያ፣ ወርቁ ዳመና ከነቤተሰቦቹ ከሞንትርያል ካናዳ። እኔም ከነቤተሰቤ ከቺካጎ ሁላችንም መጣን ተሰበሰብን። ያቺን ትንሽ የሆቴል ክፍል አጨናነቅናት፣ አሞቅናት። ጨዋታውም እየደራ ነው። በዛች ትንሽ ክፍል ውስጥ የነበረው ሳቅ ጨዋታ ምኑ ተይዞ ምኑ ተነስቶ በእያንዳንዳችን ላይ ይታይ የነበረው ደስታ እንዴት እንደምገልፀው ቃላቶች ያጥሩኛል።

የማይደርስ የለምና በናፍቆትና በጉጉት ስንጠብቀውና ስናልመው የመገናኛችን ቀንና ሰዓት ደረሰ። አዳራሹ በቀበና



ኮርያ ሰፈርና በአካባቢው የሚገኙ ታሪካዊና ታዋቂ ቦታዎችንና ሌሎች ትዝታዎችን በሚያመላክቱና በሚያስታውሱ ጽሁፎችና ምስሎች አሸብርቋል። ቃዲ ደጅ፣ ሐኪም ሜዳ፣ ጃንሜዳ፣ ሻንቆ ሱቅ፣ ሙደሲር ሱቅ፣ አባ ንጉሴ፣ ጥንስስ፣ ዱቤ ባህር፣ ብስኩት፣ መስተዋት፣ አሞራ ገደል፣ ሸክላ ሜዳ፣ ኖራ ሜዳ፥ ቅንብቢት፣ አስቴር ሱቅ፣ ጉልት፣ አዴ ከበደ፣ ዕድር ት/ቤት ፣ ቃኛው በኮርያ፣ እማማ ዲንቃ ቤት፣ አምሳለ ቤት፣ ዱረቲ ቤት፣ ቤላ፣ አባ ክበድ ሜዳ፣ ደያስ፣ ከድር ሱቅ፣ ለማ ግሮሰሪ፣ ካሌብ አደባባይ፣ አቦል ሱቅ፣ ገረመው ግሮሠሪ፣ ወንድሙ ስጋ ቤት ፣ ጤና ቡድን፣ ደብሪቱ ጠጅ ቤት፣ መሰሉ ጠጅ ቤት፣ ጥምቀተ ባህር፣ አባ አብደላ ሻይ ቤት፣ ሸለቆ ፓስቲ ቤት፣ ካራ ማራ ፎቶ ቤት፣ አሰፋ ፎቶ ቤት፣ ገድሌ ምንጭ፣ ኩባ ግቢ፣ ላይ ጫካ፣ ዶሮ ተራ፣ ቡሄ ቡሄ በሉ፣ ዕንቁጣጣሽ፣ አሲዮ ቤሌማ፣ ቃብ ስል ቀብ ነው እና ሌሎችም፤ ዝርዝሩ፣ ማስታወሻው ይቀጥላል። የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትና የቀብር ሰነስርዓት እንኳን ሳይደረግላቸው የተለዩን ወንድሞቻችን ስምም በግድግዳው ላይ በርካታ ቦታ ላይ ጎላ ብለው ይነበባሉ።

ከቀኑ 6ሰዓት የአዳራሹ በር ተከፈተ። እንግዶችም በተዘጋጀው የክብር መዝገብ ላይ ስማቸውንና አድራሻቸውን እያሰፈሩ ወደውስጥ ይገባሉ። በእያንዳንዱ እንግዳ ፊት ላይ የሚታይው የመደንገጥና የመገረም ሁኔታ ነበር። ማን ልበል እንዴ አንተ አንቺ ጩኸት ልቅሶ። የሚያዩት ሰው ሁሉ በፊት የሚያውቋቸው የልጅነት የወጣትነት ሳይሆን በእድሜ ጠና መለጥ፣ ሸበት፣ ወፈር፣ ቀጠን፣ አጠር የጊዜውን እርዝማኔ የሚናገሩ ነበሩ። መጮህ፡ መሳቅ፡ ማልቀስ እንደው ምኑ ቅጡ አንዱን ሳይጨርሱ ወደ አንዱ መዝለል አቤት ደስ ሲል። ቀበናዊ ናፍቆት ቀበናዊ ትዝታ፤ ጨዋታ ቀበናዊ ፍቅር ባጠቃላይ ቀበናዊ ቤተሰባዊነት። ልጆች ሲሮጡ ሲሮጡ ሲሯሯጡ ማየት ራሱን የቻለ ትዕይንት ነበር።ለምን ያህል ጊዜ ተራርቀን እንደቆየን የሚታዩት ሁኔታዎች ሁሉ ታላቅ ምስክሮች ነበሩ።

አዳራሹ ወደ መሙላቱ ላይ ነበር። እንግዶቹ እንዲቀመጡ ከተደረገ በኋላ የእለቱን ዝግጅት በሚመለከት ሰለሞን ሀድጎ የእንኳን ደህና መጣችሁና ዝግጅቱን በሚመለከት አጭር ንግግር ካደረገ በኋላ ለእንግዶች የምሳ ግብዣ ተደረገ። መጉረስ፣ ማጉረስ፣ መጎራረስ ቀበናዊነት፣ ቤተሰባዊነት የታየበት የምሳ ግብዣ ነበር። ይህን የምሳ ግብዣ በማዘጋጀትና በማቀነባበር ትልቅ አስተዋጽዖ ያደረጉትን ውድ የኮርያ ሰፈር እህቶቻችንን፤ በተለይም ደግሞ ፋኖስ ሃብቴንና የጋንፋሬን ውድ ባለቤት ኤልሣን ከልብ እናመሰግናለን።

ቀጥሎም የትውውቅ ጊዜ ሆኖ በመጀመሪያም የዝግጅቱ አስተባባሪዎች እራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን በተለይም ልጆች በአማርኛ እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ተደርጓል። በህይወት የሌሉትን አብሮ አደጎቻችንን በማስታወስ የህሊና ፀሎት ተደርጓል። በተለይም የቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑትን፣ የቀብር ስነስርዓት ያልተፈጸመላቸውን፣ አፈር የመልበስ እድል ያላገኙትን፣ የትም ወድቀው የቀሩትን ወንድሞቻችንን ለማስታወስ በወርቁ ዳመና የተዘጋጀ ግጥም ተነቧል። የእያንዳንዳቸው ስም እየተጠራ እንድናስባቸው ተደርጓል። እንዲሁም በአፈወርቅ መኮንን የተዘጋጀ ግጥም ተነቧል። ለነኚሁ የቀብር ወግ ማዕረግ ላላገኙት ውድ ወንድሞቻችን በስማቸው ሻማ አብርተን፣ የህሊና ጸሎት አድርሰን አስታውሰናቸዋል።

በልጅነት ጊዜያችን በተለያዩ መድረኮች ያንጎራጎሩና በድራማ የተሳተፉ ለትዝታ ያህል እንዲያካፍሉን ተጠይቀው ዳንኤል አርጋው አቫንቴን ተጫውቷል።ወደፊት የቀበና ልጆች ስብስብ ምን መልክ መያዝ አለበት? ከዚህ በኋላስ ምን መልክ ይኑረው? በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጓል። ከቀረቡት ሀሳቦች አንዱ በወይዘሮ መሠረት በቀለ የቀረበው ሀሳብ የቀበና ልጆችን ታሪክ የሚዘክርና የቀበናን ትዝታ የሚያስታውስ መጽሄት እንድናዘጋጅ የሚለው ነበር። ሁሉም በሃሳቡ ሙሉ በሙሉ ተስማማ፤ ኮሚቴውም ሀላፊነቱን ወስዶ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ቃል ገባ። ኮሚቴውንም ለማጠናከርና ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ወጣቶችና ሴቶች እንዲሰሩ ጥሪ ተደረገ። የሚቀጥለውን ዓመት የመገናኛ ቦታ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ውድድር በሚደረግበት ቦታ እንዲሆን ተወሰነ። በመጨረሻም የፎቶግራፍ ፕሮግራም ሆኖ የእለቱ ዝግጅት ተጠናቀቀ።

በአምናው ስምምነት መሰረትም እነሆ የመጽሄት ማዘጋጀቱ ነገር ዕውን ሆነ። ለዝግጅቱ ሁሉም ሃላፊነት በመውሰድ ከበርካታ ወራት ስብሰባዎች፣ ከብዙ የስልክ ጥሪዎች እና የማርቀቅ፣ የማረም ሥራ በኋላ ይህ ከቀበና ማህደር ብለን የሰየምነው መጽሄት ተዘጋጅቶ ቀረበ። የሁላችሁም የቀበና ኮርያ ሰፈር አብሮ አደጎች ጥረትና ድጋፍ የሚገኝ ከሆነ መጽሄቱ ቀጣይነት ይኖረዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

# የግል ማስታወሻ

መቼም 2005 ዓ.ም (2013) በጣም የሚገርም ዓመት ነበር ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። ለዘመናት በአብዛኛዎቻችን ልብ ውስጥ ተቀብሮ የነበረውን የተዳፈነ የልጅነትና የአብሮአ ደግነትን የትዝታ እሳት ፍም በማራገብ ማቀጣጠል የጀመርንበት ዓመት ነበርና። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

የሳሙኤል ደሬሳ ስልክ በሰፈር ልጆች ቤት ማንቃጨል የጀመረበት ወቅት ነበር። የሳሙኤልን የስልክ በረከት ከተቋደሱት አንዱ እኔም ነበርኩና። አውርተን ልንጠግብ ያልቻልናቸው የጋራ ትዝታዎቻችንን የኮመኮምንበት ዓመት ነበር። ሳሙኤል የሌሎች አብሮ አደጎቻችንን የስልክ ቁጥሮች እያፈላለገ ያንዱን ላንዱ ያስተላልፍ ነበር። እኔም የነ ጉቺ ሱራፌልን፣ የዳንኤል አርጋውን፣ የሰለሞን አስፋውን ቁጥሮች አግኝቼ ለረጅም ዓመታት ያጣኋቸውን የአብሮ አደጎቼን ብርቅዬ ድምጽ/እስትንፋስ አዳምጫለሁ። ምንኛ ያስደስት እንደነበርም መገመት አያዳግትም። ጉቺ ሱራፌል ለአብሮ አደጎቻችን ከሚደውሉትና እርስ በርስ ለማገናኘት በከባዱ ከሚጥሩት አንዱ ነበር።

ከወንድሜ ከገዛኸኝ ታደሰ ጋርም በዚሁ ጉዳይ ዙርያ ማውጋት ጀማምረናል። በተለይ በአንድ ወቅት ያልታሰበ የስልክ ጥሪ ከጉቺ ሱራፌል ካገኘ በኋላ ደውሎልኝ አንድ በጣም የሚያስደስት ሃሳብ አካፈለኝ። ይኸውም ከሰፈር አብሮ አደጎቻችን ጋር በስልክ መገናኘት ከተጀመረ ለምን በዚህ ዓመት በሰኔ ወር የመጨረሻ ሳምንት (July 2013 የመጀመሪያ ሳምንት) በሚደረገው የሰሜን አሜሪካ የመላው ኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ውድድር ጊዜ በአካል ልንገናኝ የምንችልበትን ሁኔታዎች አናመቻችም የሚል ነበር።

ሃሳቡን በደስታ ተቀበልኩት። እኔንም እስካሁን ላገኘኋቸው አብሮ አደጎቻችን ስልክ ደውዬ ሃሳቡን እንዳካፍል ጠየቀኝና ሙሉ በሙሉ ተስማምቼ በማግስቱ ተልዕኮዬን ማድረስ ጀመርኩ።

የመጀመርያ የስልክ ጥሪዬንም ወደ ጋንፋር (ሰለሞን ኃድጎ) አድርጌ ሃሳቡን ሳጫውተው እሱም የተባረከና የተቀደሰ ሃሳብ ነው ብሎ ሙሉ በሙሉ ተቀበለው። በማከታተልም ለአጥናፉ በቀለ፣ ለሳሙኤል ደሬሳ፣ ለጉቺ ሱራፌል፣ ለሰለሞን አስፋውና ለዳንኤል አርጋው ዘርዘር አድርጌ ሃሳቡን አወጋኋቸው። በሚገርም ሁኔታ ሁሉም በደስታ ተቀበሉት። ሁሉም ነገር ጊዜው ሲፈቅድ ብቻ ነው የሚሳካው የሚባለውን አባባል ሃቅ መሆኑን እንደገና መሰከርኩኝ።

ግርማ ታደሰ - ሰኔ 2006



# እስቲ እናስታውሳቸው

ይህ የመጽሔቱ ክፍል ቀበና-ኮሪያ ሰፈር አብረውን ከኖሩትና ካደጉት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መካከል በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች ከጎናችን በሞት የተለዩትን የምናስታውስበት፤ የምንዘክርበት ይሆናል።

ለዚህ የመጀመሪያ እትም የመረጥነው ደግሞ እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ1969 እና 1970 ዓ.ም. "ቀይ ሽብር" ተብሎ በሚታወቀው መንግስታዊ ግድያና አፈና ሰለባ የሆኑትን ለማሰብ ነው።




ከዛሬ ሰላሳ አምስት አመታት በፊት ያጣናቸውን ውድ ጓደኞቻችንን ለማሰብና የእያንዳንዳቸውን አጭር ሕይወት ለመዘከር ስንነሳ አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ገጥመውናል። አንዱ ችግር ስለ እነርሱ ታሪክ ሊነግሩን የሚችሉ የቅርብ ዘመዶቻቸውን ማግኘቱ ነበር። ሌላውና ዋነኛው ችግር ግን ዘመዶቻቸውን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ካገኘንም በኋላ በጉዳዩ ላይ እነርሱን ማነጋገር መሞከሩ አልቅሰው ያልወጣላቸውን የረዥም ዘመን ሀዘን መቀስቀሱ ነበር። ቢሆንም ከበርካታ ወራት ማፈላለግ፥ ማሳመንና ማስተዛዘን በኋላ በተለይም ኢትዮጵያ በሚገኙ ጥቂት አብሮ አደጎቻችን ከፍተኛ ጥረት የሁሉም ባይሳካልንም የተወሰኑትን ወንድሞቻችንን ፎቶግራፋቸውንና አጫጭር የሕይወት ታሪካቸውን ለማሰባሰብና ለማጠናቀር ችለናል።

በዚያ ክፉ ዘመን በአጭሩ የተቀጩ ውድ ወንድሞቻችንን ፎቶግራፍ፥ ታሪክና መጨረሻቸውን የተመለከቱ መረጃዎች የማሰባሰቡ ጥረት የሚቀጥል ይሆናል። ምክንያቱም ግልጽ ነው። እኒያ የዚያ ዘመን ሰለባዎች ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ መልካም ያስቡ የነበሩ፥ ለአገራዊ ፍትህና እድገት የቆሙና በዚያም ዓላማቸውና ተግባራቸው መስዋዕት ስለሆኑ ስማቸው በታሪክ እንዳይረሳና መጪው ትውልድ እንዲያስባቸው የማድረግ ሃላፊነት እንዳለብን ስለሚሰማን ነው።

ለዚህ እትም የበቁትን የውድ ወንድሞቻችንን ፎቶግራፎችና እነርሱን የተመለከቱ አጫጭር ዘገባዎች በመስጠትና በማሰባሰብ ለተባበራችሁን ሁሉ ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው። ወንድሞቻችን አሰፋ ለገሰ፥ ሽመልስ ሀይሉ፥ ወንድማገኝ ተሾመ፥ ደረጀ አየለ፥ አሰራት አለማየሁ፥ አማረ ጥሩሰው እና ታምራት ሞላን በተለይ ልናመሰግን እንወዳለን። በእናንተ ጥረትና በዘመዶቻቸው መልካም ትብብር ይህን ለመጪው ትውልድ ቀሪ የሚሆን የጽሑፍ ቅርስ አዘጋጅተን አቅርበናል።



የህሊና ፀሎት . . .

## የሩቅ፤ ቅርብ ሃዘን

የሩቅ፤ ቅርብ ሃዘን
በሉ እንዘክር አብረን፤
እናንት ሰማዕታት  እንደምን አላችሁ ?
ከዓመታት በኋላ፤ ይኸው አሰብናችሁ
በአሜሪካ ምድር፤ ቀሪው ዘከራችሁ
ከእነ ልጆቻችን፤ ዛሬ አስታወስናችሁ።
ባልንጀሮቼ ፤ ቁሙ በተራ
አብሮ አደጎቼ፤ ቁሙ በተራ
ጎልማሳዎቹ ፡ ወጣት ልጆቼም ፤ ቁሙ በተራ
የሰማዕታቱን  ስም፤ አንድ በአንድ እንጥራ።
ጌትነት የማነ፤ አንተ ፈር ቀዳጅ
የየካቲት ቤዛ፤ የቀበና ልጅ።
ከፍያለው ይሉህል ቤተሰቦችህ
በእኛም በኩል ቢሆን ከፍ እንዳልክ ነህ።
የቀበና ውኃ፤ የዱቤ ባህር
አላየኸውም ወይ አክሊለ አባተን ?
የቀበና እናቶች ዘቅዝቁ ነጠላ
ለቆራጥ ልጃችሁ ለሙሉጌታ ሞላ።
ዴቭል ነው ይሉታል፤ እውነትም ዴቭል
ፍርሃት የማያውቅ ለሕዝብ ሲታገል
እንደወጣ ቀረ በዚያ መራር ትግል።
ብርሃነ ከበደን ማን ያውቃል በሠፈር
ዕይታን ሳይፈልግ የሞተ ለሃገር።
በለጠ፤ ኃብታሙ፤ የአቶ አየለ ልጆች
ለቀበና፤ ጎንደር የሆኑ ቤዛዎች።
ጎንደር ምን አወራ፤ በለሳ ጠለምት
ውርዬ መኮንን በክብር ሲሞት።
የሰው በላ ዘመን፤ ፍቅር ያልታደለ
እስቲ እንዴት  ጨከኑ? በዘውዱ በቀለ።
አብዮት ዕብደት ነው ስሜት የሚያጋግል
ስለምን ይሞታል? ከበደ አጎናፍር ።
በአበሻ አገር፤ በምድረ አበሳ
ተሰቃይቶ አለፈ፤ ፀጋዬ ቶሎሳ።
አማኑዔል ጓዴ “አንቺ” የምልሽ
ሁሌ ይናፍቀኛል ደጉ ፈገግታሽ።
ታሪክ ጠይቅልኝ አፋኝ ስኳዱን
የት እንዳደረሰው ፍቃዱ ማሞን።
ሐምሌ  ፲፰ ምሽት የጎዶሎ ቀን፤
እንጫወት ነበር የወጣት ወጉን፤
ከጎኔ ሲነጥቁኝ፤ ፍቄና አሥማረን።
በሞቴ ጸጥ እንበል ፤ እስቲ አንዴ እናስታውስ
ከሁሉ ተግባቢ አሥማረ ሃጎስ
ፍቃዱ ማሞንም የኳስ መሃንዲስ ።
ሐምሌ ፲፰ ምሽት ጩኸት በረከተ፤ ተኩሱ በረከተ፤
በግርግሩ ውስጥ፤ ጋሽ ጥላሁን ሞተ።
ስንቱን ስሙን ልጥራ፤ ስንቱን ላስታውሰው፤
ሞገስ ማሞ በሉ የሽክላ ሜዳው።
ያንን ታጋይ ትውልድ ወቀሳ አታብዙበት
ፍትህ በማለቱ፤ ደም በገበረበት።
አይዞህ አንተ ትውልድ፤ ቀና በል ወገኔ
ከሕዝብ ጎን መቆም ፤ የለውም ኩነኔ ።
ጥሩንባ አልተነፋ፤  ቀብር አልተወጣ፤ ተዝካርም አላየን፤
በአጭሩ ሲቀሩ አብሮ አደጎቻችን፤
በቀረን አማራጭ፤ ከመንፈሳቸው ጋር ብዙ ዓመታት ኖርን።
ህይወት ጎዶሎ ነው፤ ለቀረነው ጉላ፤
ጓደኞች ላጣነው፤ በቀይ ሽብር ዱላ ።
እኒህ ከዚህ በላይ  የዘረዘርኳቸው፤
በግፍ የተቀጩ፤ ሰማዕታት ናቸው፤
ከእኛ ከተለዩ፤ ከሰላሳ ዓመታት፤ በላይ የሆናቸው።
ከዚያም ወዲህ ቢሆን አጥተናል በርካታ
የቅርብ ጓዘናችን የእኛ ሮዛ ደስታ ።

ወርቁ ዳመና
ጁላይ 6 ቀን 2013 (እ ኤ አ)
ሜሪላንድ፤ አሜሪካ

# ሙሉጌታ ሞላ (1947-1970)



በሰፈር የቅጽል ስሙ “ዴቭል” ይባል ነበር፤ ከልጅነቱ ጀምሮ በማንኛውም ፍትሃዊነትና ሚዛናዊነት በጎደለው አካሄድና አሰራር ላይ ከነበረው የማይበገር ባህሪው ጋር የሚስማማ የቅፅል ስም።

ሙሉጌታ ተወልዶ ያደገው በቀበና ኮሪያ ሰፈር ውስጥ ልዩ መጠሪያው “ሸክላ ሜዳ” በሚባለው አካባቢ ነበር። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ያጠናቀቀው በቀድሞው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሲሆን፥ በ1969 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአንደኛ አመት ተማሪ ነበር።

ሙሉጌታ በምክሩ፥ በቁጣው፥ በቀልዱና በወኔው ማንኛውንም ሰው ወደእርሱ የመሳብና የማሳመን ፀጋን የተላበሰ ሰው ነበር። በአካባቢው የሸክላ ሜዳ ልጆች እንደ ታላቅ ወንድም የሚከበር፥ በመላው የሰፈሩ ልጆች ደግሞ ከህዝብ ወግኖ የመቆም አርዓያነትን ያሳየ፥ ወጣቶችን ለማህበረሰባዊ ፍትህና ለነጻነት እንዲቆሙ ያበረታታ አና ያደራጀ የቆራጥ ታጋይ ተምሳሌት ነበር።

ሙሉጌታ ሞላ የኢትዮጵያ አብዮት በ1966 ዓ.ም. ሲቀጣጠል የ19 አመት ወጣት ነበር። በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴም ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነበር። ፊውዳላዊው ስርአት በአብዮቱ ተወግዶ ወታደራዊ መንግስት ስልጣን እንደያዘ ሙሉጌታ እንደ ሌሎች የኢትዮጵያ ወጣቶች ሁሉ ዲሞክራሲያዊና ህዝባዊ መንግስት እንዲመሰረት በወቅቱ በፖለቲካ ፓርቲ ተደራጅተው ከታገሉት የዚያ ትውልድ አባሎች አንዱ ነበር። በዚያ ተሳትፎውም ምክንያት በወታደራዊው መንግስት ካድሬዎችና የደህንነት ሰራተኞች ከፍተኛ ክትትል ይደረግበት ነበር።

በአዲስ አበባ ውስጥ ተሰውሮ መኖር ለአደጋ ያጋለጠው በመሆኑ በአንድ ወቅት ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ገጠራማ ስፍራ በገበሬዎች መንደር ውስጥ ከሌሎች የትግል ጓዶች ጋር ተጠልሎ ቆይቷል። ይሁንና ያም መጠለያ ባልታወቀ ሁኔታ በወታደራዊ መንግስት የደህንነት አባላት ተጋልጦ አንድ ምሽት ተከብቦ ከተከፈተ ተኩስ ውስጥ ሙሉጌታ በማምለጥ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተመልሶ በመግባት በድብቅ ለተወሰነ ጊዜ ኖሯል። በማምለጡ ሂደትና በረዥም የእግር ጉዞ ሳቢያ በደረሰበት ጉዳት ለተወሰነ ጊዜ በጥቂት የቤተሰቡ አባላት በተደበቀበት ስፍራ ሲጠየቅና ሲረዳም ቆይቷል።

ሙሉጌታ በከተማው የጸጥታ ሁኔታ በነፃ መንቀሳቀስ ባለመቻሉና ከፍተኛ የትግል ስሜቱንና ሃላፊነቱን ለመወጣት በሚል ወደ ሜዳ የትጥቅ ትግል እንደተሰማራ ይገመታል። ሙሉጌታ በአገሩ የተሻለ ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወትን ለማስፈን በተደረገው እንቅስቃሴ አብዛኛውን እድሜውን ያሳለፈና በመጨረሻም በ1970 ዓ.ም. ውስጥ ከፍተኛውን መሰዋእትነት በህይወቱ የከፈለ ወጣት ነበር።

# ብርሃነ ከበደ (1940 - 1970)



ብርሃነ ከበደ ከአባቱ ከአቶ ከበደ እንዳለው እና ከእናቱ ከወ/ሮ ጥሩነሽ ለታ ጥቅምት 5 ቀን 1940 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በአስፋወሰን፥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በቀድሞው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት አጠናቅቆ ከፍተኛ ውጤት በማግኘቱ በልኡል በእደ ማሪያም የሙከራ ትምህርት ቤት ገብቶ በአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናም ቀደም ሲል ያስመዘገበውን ከፍተኛ ውጤት በመድገም ለከፍተኛ ትምህርት በቀድሞው ሃይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ ኢዱኬሽን ፋኩልቲ በጂኦግራፊ ክፍለ ትምህርት ተመዘገበ። ትምህርቱን ለአንድ አመት ተኩል ከተከታተለ በኋላ በራሱ ፍቃድ የዩኒቨርስቲ ትምህርቱን በማቋረጥ በአስተማሪነት ስራ ተሰማራ። ይሁንና ትምህርቱን በማታው ክፍለ ጊዜ በመቀጠል በማህበራዊ ስራ ዘርፍ በዲፕሎማ ተመርቋል።

ብርሃነ ከልጅነቱ ጀምሮ የቅድስት ስላሴ ካቴድራል የሰንበት ት/ቤት አባል የነበረ ሲሆን፤ የሰንበት ማህበሩ ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆንም አገልግሏል። ብርሃነ በ1963 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሀዋሪያው ድርጅት በጊዜያዊ ሰራተኛነት፥ ከመስከረም 1964 እስከ ታህሳስ 1967 ዓ.ም. ሰበታ በጌቲ ሰማኔ ት/ቤት በዳይሬክተርነት፥ እና ከጥር 1967 ዓ.ም. ጀምሮ በቅድስት ስላሴ ት/ቤት በዋና ጸሀፊነት በመጨረሻም በርእሰ መምህርነት አገልግሏል። በነዚያ ዘመናት ለቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያንና ለት/ቤቱ እድገት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ብርሃነ ለቤተሰባዊና ማህበራዊ ህይወት ክብር የነበረው፥ ከራሱ ይልቅ የሌሎችን ምቾት የሚያስቀድም፥ በመምህርነት ሙያው ተጠቅሞ መልካም ዜጎችን ለማፍራት የጣረ ሰው ነበር። ለእናቱና አባቱ፥ ለእህቶቹና ወንድሞቹ ከፍተኛ ፍቅር የነበረው መከሪያቸውና መላ ቤተሰቡን በሚያገኘው ደሞዝ የሚረዳ፥ በከፍተኛ የሞራል ሰብእና የታነጸ ሰው ነበር።

ብርሃነ ከወታደራዊው አገዛዝ ነጻ ለመውጣት በተደረገው ትግል ከፍተኛ ድርሻ የነበረው ሲሆን፤ መኪና ቤትና ሌላ የግል ንብረቱን ለትግሉና ለትግሉ አጋሮቹ መጠቀሚያነት ያዋለ ሰው ነበር። በዚህ ተሳትፎው በደርግ የደህንነት ሰዎች ተጠርጥሮ በየካቲት ወር 1970 ዓ.ም. በርእሰ መምህርነት ከሚያገለግልበት የቅድስት ስላሴ ት/ቤት ተይዞ ወደ ደርግ ጽ/ቤት ከዚያም ወደ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ እያዘዋወሩ በምርመራ ሲያሰቃዩት ከቆዩ በኋላ መጋቢት 20 ቀን 1970 ዓ.ም. ልብሱን ለቤተሰቡ በመመለስ ሞቱን አረዱቸው። ብርሃነ ከበደ በደርግ የደህንነት ሰዎች አሰቃቂ ድብደባ በተወለደ በ30 አመቱ በሞት ቢለይም በመልካም ስነ ምግባሩና ለህዝብ ነጻነት በመቆሙ በቤተሰቡ፤ በጓደኞቹና በማህበረሰቡ ብሎም በታሪክ ሁሌም ሲታወስ ይኖራል።

# ዘውዱ በቀለ በየነ (1946 - 1970)



ዘውዱ በቀለ ከእናቱ ከወ/ሮ ተዘራ ሀይሌና ከአባቱ ከአቶ በቀለ በየነ ጥር 4 ቀን 1946 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ለቤተሰቡ ሶስተኛ ልጅ ሆኖ ተወለደ።

ዘውዱ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የተከታተለው በዳግማዊ ምንሊክ ት/ቤት ሲሆን የሂሳብ አያያዝ ትምህርት ተከታትሎም አጠናቋል። ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በተካሄደው "የእድገት በህብረት፥ የእውቀትና የስራ ዘመቻ" ውስጥ በመሳተፍ በትግራይ ክፍለ ሀገር ፈረስ-ማይ በሚባል ቦታ ዘምቶ ኢትዮጵያዊ ወገኖቹን በማስተማርና በዚያ አካባቢም ሆነ በመላው ሃገሪቱ ውስጥ መልካም አስተዳደር ይሰፍን ዘንድ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ህዝቡን በማስተባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ዘውዱ በጸባዩ ለስላሳና ከሁሉ ጋር ተግባቢ ነበር። ትርፍ ጊዜውን መጻህፍት በማንበብና ቤተሰቡን በመርዳት ማሳለፍም ይወድ ነበር።

ዘውዱ ለህዝብ መብትና ነጻነት በነበረው እምነትና የፖለቲካ አመለካከት በወቅቱ በስልጣን ላይ በነበረው ወታደራዊ መንግስት ጋሻ-ጃግሬዎች ክፉ እይታ ውስጥ በመግባቱ ከመጋቢት እስከ ሰኔ 1969 ዓ.ም. ለሶስት ወራት ያህል ታስሮ ተፈትቶ ነበር። ዘውዱ በቀለ በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ከፍተኛ ክትትል ይደረግባቸው ከነበሩት ወጣቶች መካከል አንዱ ስለነበረ፣ የሚኖርበትን አካባቢ ቀይሮ በሌላ ሠፈር ይኖር ነበር። በጥቅምት 1970 ዓ.ም. መጀመርያ ላይ በአዲስ አበባ ስታዲዮም አካባቢ የከፍተኛ 13 ቀበሌ 06 ካድሬዎች ተከታትለው ከያዙት በኋላ ለደርግ ጽህፈት ቤት ልዩ ምርመራ ክፍል አሳልፈው ሰጥተውታል። ከዚያም በዚሁ በደርግ ጽ/ቤት በግርፊያ ሲሰቃይ ቆይቶ በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ጥቅምት 12 ቀን 1970 ዓ.ም. ህይወቱ አልፏል።

# ፍቃዱ ማሞ (1954 – 1969)



## የፍቃዱ ማሞ አጭር የህይወት ታሪክን በተመለከተ ከእህቱ ወ/ሮ አዳነች ማሞ ጋር ቃለ-ምልልስ

የፍቃዱ ማሞን አጭር የህይወት ታሪክ እንድትነግረኝ እህቱን ወ/ሮ አዳነችን በስልክ ነበር የጠየቅኳት። እጅግ ከባድ ነገር ስለነበር በአካል ማግኘትና ማወያየት አልቻልኩም። ተቀብሮ የሚኖርን ሀዘን መቀስቀስ ሆኖ ስለሚሰማኝ። ግና አላማው ስሙን ለመዘከርና ለአዲሱ ትውልድ ለማስተላለፍ እንደሆነ ከወንድሜ ወርቁ ዳመና ተገልጾልኝ ስለነበር ማሳካት እንዳለብኝ አምን ነበር።

ከታላቅ እህቱም ፎቶግራፉን ስቀበል እመለከት የነበረው የሀዘን ስሜት ጉዳዩ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለመረዳት አላዳገተኝም። አሁንም በስልክ ሳነጋግራት ይታሰበኝ የነበረው ስሜት ያው የተቀላቀለ ነበር። እሷም በጉዳዩ ላይ ገፍታ ለመነጋገር አትደፍርም። ምክንያቱም ወንድም፤ ያውም በሩቅ ሲያልም በአጭርና በአፍላው የተቀጨ ውድ ወንድሟን ያጣች በመሆኗ. . .ለማንኛውም ውይይታችንን ጀመርን. .

ጥያቄ- ወ/ሮ አዳነች መቼም አንቺ እያልኩ ነው የማናግርሽ ታላቅ እህታችን ነሽና. . . እንደው እስቲ የእናትና አባታሽን ሙሉ ስም በመንገር ታሪኩን ብትጀምሪልኝ!

ወ/ሮ አዳነች፡- አባታችን አቶ ማሞ ተሰማ እናታችን ወ/ሮ አበራሽ አልማው ይባላሉ።

ጥያቄ- ፍቃዱ ማሞ መቼ ተወለደ?

ወ/ሮ አዳነች፡- ቀኑን ወሩንና ዓመተ ምህረቱን በዚህ ጊዜ ነው ብዬ ለመናገር አላስታውሰውም፤ ግን እኔ አሁን ዕድሜዬ 54 ደርሷል። ወንድሜ ፍቃዱ ደግሞ የኔ ታናሽ ሲሆን የምበልጠውም በሁለት ዓመት ነው። እንግዲህ እግዜር ፈቅዶ ለዛሬ ደርሶ ቢሆን ኖሮ 52 ዓመቱ ይሆን ነበር። ምን ዋጋ አለው በአጭሩ ተቀጨ። ዝምታ. . . በትዝታ ወደኋላ ጉዞ. . .

ጥያቄ- ፍቃዱ የት ተወለደ፣ ዕድገቱስ የት አካባቢ ነበር፣ ትምህርትስ የት ጀመረ?

ወ/ሮ አዳነች፡- ፍቃዱ የተወለደው ቀበና ኮርያ ሰፈር ነው። ከዕድሜ እኩዮቹ ጋር እዚሁ ሰፈር ተጫውቶ ያደገ ሲሆን፤ ትምህርቱንም ከአንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ የዘለቀው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነው።

ጥያቄ- እስቲ ወደአስከፊውና ለማንሳትም ወደሚከብደው ጊዜ ልመልስሽ. . . ፍቃዱ መቼ ተያዘ? የእስሩንስ ጊዜ እንዴት ታስታውሺዋለሽ?

ወ/ሮ አዳነች፡- በዝምታ ለረጅም ጊዜ ቆይታ. . . ያን ጊዜ ማስታወስ ከባድ ነው። ቀኑንም አላስታውስ። ሁሉን ነገራችንን ይዞት ሄደ እኮ. . .ግን ብቻ ጊዜው ቀይ ሽብር በሚል አገር የሚታመስበት ጊዜ እንደነበረና ቀኑም እሁድ እንደነበረ ብቻ አስታውሳለሁ. . . ተወኝ እባክህ. . .የሀዘን ዝምታ. . .በእስር በቆየባቸው ጊዜያት ለሁለት ወራት ያህል አካባቢ ስንቅ እናመላልስ ነበር፤ እንዳለም እናውቅ ነበር. . . በኋላ ላይ በሸሚዙ ኮሌታ ውስጥ ወረቀት ጽፎ ላከልን... ከሰሞኑ ወደሌላ እስር ቦታ ትሄዳላችሁ እያሉን ነው. . . ወደ ቀበሌያችሁ ትሄዳላችሁ እያሉን ነው የሚል. . .ግን ምን ዋጋ አለው. . .

ጥያቄ- ህልፈቱን እንዴት ሰማችሁ?

ወ/ሮ አዳነች፡- ህልፈቱንማ ማን በወጉ ነገረን ብለህ ነው. . . ብቻ እንደሌላው ጊዜ ስንቅ ለማቀበል ስንሄድ አንቀበልም አሉን። የስንቅ አንቀበልም ትርጉም በወቅቱ የታወቀ ስለነበር እኛም የፈራነው እንደደረሰ ተረዳን፤ እርማችንን ወደ ሆዳችን ውስጥ በማንባት አወጣን. . .በቃ እስካሁን እህህ እንዳልን አለን።

ወ/ሮ አዳነች መቼም ሀዘንሽን እንደ አዲስ ስለቀሰቀስኩብሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ ግን ስሙን ለመዘከር ስለሆነ አንቺም እንደምት ረጂልን እርግጠኛ ነኝ።

ወ/ሮ አዳነች፡- ከሰላሳ አምስት አመት በኋላ ስሙ በክብር ሲነሳ እጅግ ደስ ብሎኛል። ነግረውኛል ሰዎች፤ አንድ ዝግጅት ላይ እኒያ በአጭር የተቀጩ የቀበና ልጆች መታሰባቸውን. . . ደስ የሚል ነገር ነው። እግዜር ይስጣቸው ላሰቡት ሁሉ. . .

ወ/ሮ አዳነች ለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ። ሰላም ሁኚልን።

ታምራት ሞላ

ግንቦት 3 ቀን 2006 ዓ.ም. አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ጌትነት የማነ (1950 – 1969)



ወጣት ጌትነት የማነ ከአባቱ ከሻምበል ባሻ የማነ ተመስገን እና ከእናቱ ከወሮ ነቃገነት ጌታሁን በሰኔ ወር 1950 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። እድሜው ለትምህርት ሲደርስም በወቅቱ በቀበና አካባቢ ታዋቂ ከነበሩት የቄስ ትምህርት ቤ/ት መምህር አባ አዳነ ጋ በመግባት ከ 1955 ዓ.ም. እስከ 1957 ዓ.ም. ድረስ ትምህርቱን ተከታትሏል። ከ 1958 ዓ.ም. እስከ 1963 ዓ.ም. የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በወቅቱ የጃንሆይ ሜዳ አካባቢ ትምህርት ቤ/ት እየተባለ ይጠራ የነበረውና በአካባቢው በሚገኙ የመረዳጃ ዕድሮች ህብረት በተቋቋመው ትምህርት ቤ/ት ተከታትሏል። ይህ ት/ቤት ከዚያ በኋላ የልዑል ሣህለ ስላሴ ት/ቤት ተብሎ ይጠራ የነበረ ሲሆን ባሁኑ ጊዜ ደግሞ የህብረት ፍሬ ት/ቤት በመባል ይታወቃል። ከ 1964 ዓ.ም. እስከ 1965 ዓ.ም. የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ኮከበ ጽባሕ ት/ቤት ተከታትሏል። የ9ኛና የ10ኛ ክፍል ትምህርቱንም በዚሁ በቀዳማዊ ኃሥላሴ ኮከበ ጽባሕ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ 1966 ዓ.ም. እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ ተምሯል።

ቀበና ካፈራቻቸው ጀግኖች ፣ ኢትዮጵያ ካበቀለቻቸው ቆራጦችና ስማቸው በታሪክ መዝገብ ላይ በወርቅ ቀለም ከሚጻፉት አንዱ ነው፤ ጌትነት የማነ። ጌትነት ገና ከህፃንነቱ ጀምሮ በትምህርቱ፣ በትህትናው፣ በስፖርት ችሎታው እንዲሁም በተግባቢነቱ የሚታወቅና የሚደነቅ ዕንቁ ነበር። ባጭሩ ምግባረ ሰናይ። በያዘውና በገባበት ነገር ውስጥ ሁሉ ቀንጮ ነበር። በትምህርቱ አንደኛ፣ በእግር ኳስ ጨዋታ የሚስተካከለው የሌለ፣ በአክሮባትም ይሁን፣ በዋና፣ በጠረጴዛ ኳስ ይሁን በመረብ ኳስ፤ ብቻ ጌትነት በነካው ነገር በሙሉ ተወዳዳሪ አይገኝለትም ነበር። ጀግና፣ ደፋር፣ ርህሩህና ታናናሾቹን በሙሉ በፍቅር የሚወድ ፣ የሚያከብርና የሚንከባከብ ልዩ ፍጡር ነበር። ግና ምን ይደረጋል . . .

የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ
ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ

በጌትነትና በጓደኞቹ እድሜ የነበሩ ወጣቶች ወይም ጎረምሶች ለወትሮው አዋዋላቸው የታወቀና የተለመደ ነበር። ጌትነትና ጓደኞቹ ግን የታሪክ አጋጣሚ ሆነና በዚያ በለጋ ዕድሜያቸው የሃገርና የህዝብ ጉዳይ ያገባናል በማለት የጉርምስናውንና የወጣትነቱን ሥራም ሆነ ወግ እርግፍ አድርገው፣ ትናንት በቀበና ጎዳናዎች ላይ ለብይና ለጠጠር ብለው እንዳልተፈናከቱ፣ በኳስ ጨዋታም ሆነ በቡሄው ላይ እንዳልተጋጩ፤ ሁሉንም ትተውና እረስተው እጅ ለእጅ ተያይዘው እሩቅ ማየት፣ ትልቅ ማለም ጀምረው ነበር። ቁምነገርና ጀግንነት ተላብሷቸው ነበር። የልጅ አዋቂዎች ። ምትክ የለሽ ብርቅየዎች።

ፍጹም ነው እምነቴ
የትግሉ ነው ህይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና
በተሰዉት ጓዶች ፋና

ጌትነትም የታሪክ ባለአደራነቱን አምኖና ተቀብሎ ድርሻውን ለመወጣት የልጅ አስተዋይ፣ የልጅ ጀግና፣ የልጅ ፊታውራሪ ሆኖ ገና በጧቱ፣ ገና በመጀመሪያው ነበር ግንባር ቀደም ሆኖ ለህዝብ መብትና ነፃነት እምቢ አሻፈረኝ ብሎ የተነሳው። አምባገነኖቹ ግን በስልጣናቸው ላይ ለመሰንበት ያልፈጸሙት አረመኔያዊ ተግባር አልነበረም። ህፃኑን ከአዋቂ፣ ሴቱን ከወንድ ወይም ጎልማሳውን ከአዛውንት ሳይመርጡ ፣ ሳይለዩ ነበር በጭፍን ህዝቡን የጨፈጨፉት። ወጣት ጌትነት የማነም ገና የተደራጀው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ሀ ተብሎ ከመጀመሩ ነበር የዚሁ አምባገነን ሥርዓት ሰለባ የሆነው። ቀኑም የካቲት 28፣1969 ዓ.ም. ነበር።

ጌትነት አሁን አጠገባችን የለም። የእሱና የጓደኞቹ ስም ፣ ወደር የማይገኝለት ጀግንነታቸውና ሥራቸው ግን ዝንተ ዓለም ሲዘከር ይኖራል። አሁን በህይወት ያሉት ባልንጀሮቻቸውና አጋሮቻቸው እንዲሁም ተተኪው ትውልድ የነጌትነትን አርዓያ በመከተል ለህዝብ መብትና ነፃነት ፣ ለአገር አንድነት፤ ለፍትህና ለእኩልነት በመቆምና በመስራት ብቻ ነው የነጌትነትን ህያውነት ሊያስመሰክሩ የሚችሉት።

## ከበደ አጎናፍር (1952 - 1970)



ከበደ አጎናፍር ከእናቱ ከወ/ሮ ማሚቴ ዳኜና ከአባቱ ከሃምሳ አለቃ አጎናፍር ደምሴ የካቲት 13 ቀን 1952 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አራት ኪሎ አካባቢ ለቤተሰቡ አራተኛ ልጅ ሆኖ ተወለደ።

ከበደ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በኮከበ ጽባህ ት/ቤት ተከታትሎ አጠናቋል። በስፖርት በተለይም በእግር ኳስ ጨዋታ ፍቅሩና ችሎታው፤ እንዲሁም በአስቂኝ ቀልዶቹ የታወቀ፤ ሁሌም ፈገግታ የማይለየው ወጣት ነበር። ከበደ ቤተሰቡን በልዩ ልዩ መንገዶች መርዳትም ይወድ ነበር።

አንድ ቀን የተለመደ የስፖርት ልምምዱን ለማድረግ ከቤቱ ወጥቶ በመንገዝ ላይ እንዳለ ነው በደርግ የጥበቃ ሀይሎች ታፍኖ የተወሰደው። ከጥቂት ጊዜ በኋላም “ነጻ እርምጃ” ተብሎ ይታወቅ በነበረው የደርግ አረመኔአዊ በትር የካቲት 23 ቀን 1970 ዓ.ም. የእርሱና የሌሎች ወጣቶች ህይወት ማለፉ ታወቀ።

## ሀብታሙ አየለ (1947 -1969)

መምህር ሀብታሙ አየለ እንየው ከአባቱ ከአለቃ አየለ እንየውና ከእናቱ ከወይዘሮ አዳም ተመስገን ጥቅምት 5ቀን 1947 ዓመተ ምህረት ተወለደ። እድሜውም ለትምህርት ሲደርስ በኮከበ ጽባሕ የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቋል። ከዚያም ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ተመርቋል። ከተመረቀ በኋላም በጎንደር ክፍለ ሀገር በአስተማሪነት ተመድቦ ያስተምር ነበር። የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባል ሆኖ በሀገራችን የሚካሄደውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ በመደገፍ እና ወታደራዊውን የአምባ ገነን መንግስት ለመጣል በተደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋፅዖ የነበረው ወጣት ነበር።

በህዳር ወር በ1969 ዓመተ ምህረት የደርግን መንግስት በመቃወም በተደረገው ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ነበር የወታደራዊ መንግስቱ ቀኝ እጅ የነበረው የነበልባል ጦር በሰላማዊው ሰልፈኛ ላይ በከፈተው የተኩስ እሩምታ ሀብታሙ አየለ እና በርካታ ንፁሀን ዜጎች የተገደሉት። መምህር ሀብታሙ በሰፈራችን ውስጥ የሚታወቀው በሰው አክባሪነቱ ፣ በታዛዥነቱ ፣ በሩህሩህነቱና ለሰው ባለው ፍቅር ነበር። እግር ኳስ መጫወት የሚወድ በትምህርቱም ጎበዝና ታታሪ ነበር። ሀብታሙ አየለ በህዳር ወር 1969 ዓመተ ምህረት ውድና ክቡር ህይወቱን ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነትና ፍትህ ከፍሏል።

## በለጠ አየለ (1953-1969)

በለጠ አየለ እንየው ከአባቱ ከአለቃ አየለ እንየውና ከእናቱ ከወይዘሮ አዳም ተመስገን ጥቅምት 9 ቀን 1953 ዓመተ ምህረት ቀበና ልዩ ስሙ ኮርያ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው ቦታ ተወለደ። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በእድር ትምህርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ድረስ ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለ በአገራችን ላይ ያንዣበበውን ለውጥ ተከትሎ የስልጣን ኮርቻን የጨበጠው ወታደራዊ መንግስት በህዝብ ላይ የሚያደርሰውን የግፍ በደልና ጭቆናን በመቃወም ለነፃነት ለመብትና ለህዝባዊ መንግስት መቋቋም ከሚታገለውና ህዝባዊ በሆነው የፖለቲካ መስመር በመሰለፍ በመታገልና በማታገል ግዴታውን በመወጣት ላይ እንዳለ በደርግ ጨፍጫፊ ካድሬዎች እጅ ወደቀ፤ ታፋውን በጥይት ተመትቶ ተያዘ።

በአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ለአንድ ሳምንት በግርፋትና በድብደባ ሲያሰቃዩት በደረሰበት ከባድ ጉዳት ከአላማው ፍንክች ሳይል ገራፊዎቹን እያወገዘ ድል የህዝብ ነው እያለ አይበገሬነቱን አሳይቷል። ወደ መገደያ ቦታም ሲወስዱት በቆራጥነት ለዘመናትን የትግሉ ነው ህይወቴን እየዘመረ በ1969 ዓመተ ምህረት መጨረሻ አካባቢ በ17 ዓመቱ በአረመኔዎቹ ጥይት ተገደለ።

በለጠ በአላማው ፅኑ እምነት የነበረው ቆራጥ ጠንካራ ሀገሩንና ወገኑን ወዳድ ወጣት ነበረ። አሁንም በለጠ እና ጓዶቹ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ያሰሙት ድምፅ ከመቃብር በላይ ይጮህል።

አዎ፣ የታጋይ ድምፅ ይጮህል፤ ይጮህል ከመቃብር
ትግሉን አፋፍም ይላል አደራ ይላል ከምር።

# A NOTE TO OUR CHILDREN, TO THE VERY YOUNG

In this chapter, we tried to share stories remembering the short but eventful lives of our peers, our brothers who paid the ultimate price for standing and fighting for a just society during one of the very shining but at the same time dark moments in Ethiopia's history. It is about a generation of young people who grew up together in the same neighbourhood in Addis Ababa, Kebena - Korea Sefer.

When we grew up in that little corner of Addis Ababa, known as Kebena, Korea Sefer, we had very little, in material sense. We were, however, very close knit community who were happy, proud, strong and optimistic souls in the face of adversity.

Our happy teenage life did not last long however. There was a revolution in our country that started in 1974 – a radical social upheaval and process of change.

Almost every young people in our neighbourhood began playing, as all others around the country, one or other roles in that difficult process of change. We all were idealists, dreamers of a transformed Ethiopia. We shared one common value and aspiration i.e. to see a prosperous country, a more equitable and just society.

However, because we Ethiopians, as people, did not have a long standing tradition of handling political differences in a peaceful manner, things quickly turned violent. Political killings and persecutions engulfed our country, our neighbourhood. Sadly, not all of the boys from our neigbourhood survived that brutally violent period of our country.

After more than thirty years, we are now having a rare opportunity for us to remember and pay tribute to those whose life was cut short during that dark period. Those people who died between 1977 and 1978 did not receive any funeral. No one has information where their final resting places were. Their families were not even allowed to mourn their losses. The survivors have, therefore, a solemn responsibility to individually and collectively remember those magnificent souls who departed us over 35 years ago. Those of us who are from that era and who are still alive are lucky not only to survive the guillotine of the 1970s but also to be able to establish families.

We all have our roots in Kebena, Janmeda, Koreasefer, different names of the same place, more or less. We wish our children to know where we, their parents, came from. From the life we lived, we want you to know that free, stable, peaceful, and decent living conditions are not something that you find everywhere and every time. Many aspects of human life are not and should not be taken for granted.

**Remember!!**

# ከዚህም ከዚያም

## የቀበና ትዝታ ♦ ከግጥም አምባ

### ቀበና ሰፈሬ

ቀበና ሰፈሬ እትብቴ ያለብሽ
አስቆጠርኩ ዓመታት ከራቅሁ ካጠገብሽ
እንደምን ከርመሻል? እስቲ ልጠይቅሽ
ከራቅሁሽ ጀምሮ ምን ለውጥ እንዳሳየሽ
እንዴት ነው ሁኔታሽ ዝቅ አልሽ ተሻሻልሽ
ቀነሰ ጨመረ ቁጥሩ የነዋሪሽ።
    ስምሽን መጠሪያ አርገው የሚፈሱት
    እነዚያ ወንዞችሽ በጋ ኮለል ያሉት
    ክረምት በጎርፋቸው የሚያጥለቀልቁት
    ያበረክታሉ ዛሬም አገልግሎት?
እኔማ ሳድግብሽ ያሳየሽኝ ፍቅር
ከቶ የማይጠፋ እስከ ዕለተ መቃብር
    ሜዳሽ ላይ ዘልዬ የቧረኩበት
    ከአብሮ አደጎቼ ጋር የዘለልኩበት
    የብይ ጨዋታው ሞር ይሁን ወይ ቀስት
    በመቆጠር እዳ የምገባበት።
የቡሄ ጭፈራው ዞሮ በየቤቱ
ሳንቲም በገንዘብ ያዥ፤ ዳቦውን ባንሶላ፤ በጀርባ ማንገቱ
ዳቦውንም ሸጦ፤ ሳንቲሙን ተካፍሎ፤ ቁማር መጫወቱ
ኦፕሬሽን ዳቦ፤ ወይ ፓስቴ ብስኩቱን፤ በልቶ መደሰቱ
    ይህ ባንቺ ላይ ሳድግ ያለፍኩት ሁኔታ
    ደም ስሬ ውስጥ ጠልቆ፤ አስሮኝ በትዝታ
    ሊጠፋ የማይችል ሆነብኝ በሽታ።
መስከረም ሲጠባም አደዩ መፍካቱ
የእህቶች ጭፈራን፤ ከብረው ይቆዩኝን፤ ሰምቶ መደሰቱ
ቀለም ገዝቶ መጥቶ አበባ መስራቱ
አድባርም ሲደርስ ንፍሮውን ቂጣውን ተሻምቶ መብላቱ።
        ታቦት አስገብቶ ጥምቀት በመድረሱ
        እሳት እየሞቁ ማደር በየዳሱ።
    የኳስ ጨዋታውስ፣ ወገን ተከፋፍሎ
    ማዶን፣ ሀኪም ሜዳን፣ ጃልሜዳን አካሎ
ቃኘው በኮሪያስ ሲሸነፍ ስናዝን ሲያሸንፍ ስንጨፍር
ማታ ነው ድሌ እያልን ስንገባ ከሰፈር።
    ዘፈን ትያትሩስ የምናሳያቸው
    እነ አቫንቴ ሆኑ እነሾላ ፍሬው
    በአባቱ ዳፋ በሰው ድግስ ያለው።
ይህ ባንቺ ላይ ሳድግ ያለፍኩት ሁኔታ
ደም ስሬ ውስጥ ገብቶ አስሮኝ በትዝታ
ሊጠፋ የማይችል ሆነብኝ በሽታ።
ኧረ ስንቱን ላስታውስ ካለብኝ ትዝታ
    ቀበና ላይ ሳድግ ካካበትኩት ደስታ
    ጊዜው ሳይቀየር ሀዘን ሳይበረታ
ወላጅ ልጁን አጥቶ ምሬቱ ሳይበዛ
ጓደኞች ሳያልቁ ሳይረግፉ እንደዋዛ።
    ጌትነት የማነ፣ በለጠ አየለ፣ ያ ሞገስ ማሞና ፀጋዬ ቶሎሳን ገና ሳናጣቸው
    አክሊለ አባተን፣ ዘውዱ በቀለና ሙሉጌታ ሞላን ሳናለቅስላቸው
    ብርሃነ ከበደ፣ ከበደ አጐናፍር፣ አስማረ ሀጎስን ቀብር ሳንቀብራቸው
    አማኑኤል ሣህለማሪያም፣ ወንድምአገኝ መኮንን፣ ያ ፈቃዱ ማሞን
ብናኝ አፈር እንኳን ሳንበትንላቸው፤
ጊዜው ሳይፈቅድልን ወግ ባናሳያቸው
ቢለዩም ከመሃል ባይኖር አካላቸው
ምን ጊዜም ቀበና ነውና እትብታቸው
ዘለዓለም ይቆያል ከኛ ትዝታቸው
ሁሌም የቀበና ቤተሰቦች ናቸው።

ሰለሞን (ጋንፋር)

# የቀበና ትዝታ ♦ ከግጥም አምባ

## እነማን ነበሩ

የነጋድራስ መንደር የበቅሎ ማደሪያ
የሀኪም ወርቅነህ የመስክ ማከሚያ
ባይታወሰንም  ጊዜና ዘመኑ
    በቀበና ዙሪያ ሰፍረው የነበሩ
    እስቲ በዚያን ጊዜ እነማን ነበሩ?
የክብር ዘበኞች የኰሪያ ጀግኖች
የኮንጎ ዘማቶች ቆፍጣና ወጣቶች
    ከምዕራብ ከምስራቅ፤ ከደቡብ ከሰሜን የተሰባሰቡ
    ቀበናን ዋቢ አርገው አብረው የሚኖሩ
    እስቲ በዚያን ጊዜ እነማን ነበሩ?
በነጋድራስ ስም ዕድር የጀመሩ
ለአዲሱ ትውልድ መንገድን የመሩ
የመልካም አርአያን የእድር ት/ቤት መሰረት ያኖሩ
እስቲ በዚያን ጊዜ ያሉ ይናገሩ።
    ይቀረጽ ድምጻቸው
    ይጻፍ ታሪካቸው
    እንዲሁ እንዳያልፉ ቅርሶቻችን ናቸው።
ሆነን እንዳንገኝ የታሪክ ተወቃሽ
ዛሬ ነገ አንበል አያሻንም ቀስቃሽ።

ለአብሮ አደጎቼ የቀበና-ኮርያ ሰፈር ልጆች
አፈወርቅ መኰንን - ሎንደን
ሰኔ 28 ቀን 2006 ዓ.ም.
(July 5 2014)

## ሚሪንዳ

ኮካ በቀን ይገዛል
ፔፕሲም በቀን ይሸመታል
    ፋንታም እንዲሁ ነው
    በብርሃን ነው ገበያው
የሚሪንዳ ጣዕም በመባሱ
በጭለማ ሆነ ምልልሱ ።

ቆለኛው (ሰኔ 2006)

## ሐኪም ሜዳ

የጠዋት ፀሐይ ሳትፈነጥቅ
ከብቱ ከበረት ሳይል ብቅ
    ተጠራርተን ከየቤቱ
    ጨዋታው ይደራል በጥዋቱ
ብርድ አንል ሙቀት
ጠዋት አንል ሌሊት
    ብቻ ሁሌ ጨዋታ
    የሐኪም ሜዳ ትዝታ
ሐኪም ሜዳ ትዝታሽ
ሐኪም ሜዳ ውበትሽ
ሐኪም ሜዳ መዓዛሽ
    እግር ኳሱ፣ ቫሊ ቦሉ
    ገመድ ዝላይ፣ ዱላ ቅብብሉ
ማራቶን፣ መቶ ሜትር
የሩቅና ያጭር
ሁሉም አይነት ውድድር
    ስንፎካከር ስንጣላ
    ስንጋጭ ስንባላ
ደግሞ መለስ ብለን
ታርቀን ተስማምተን
ከውጪ አጥቂ ተጠባብቀን
ስንራገጥ እንውላለን
ደሞ ሲያሻን ወጣ ብለን
ሐኪም ሜዳን ተወት አርገን፣ ራቅ ብለን
ጋራውን ሸንተረሩን ጎብኝተን
ጥንስስና አባ ንጉሴን አዳርሰን
የድሃ ግዮናችንን፣ ዘናጭ መዋኛችንን ተሳልመን
እንመለሳለን፣ ከጉሮዷችን፣ ሐኪም ሜዳችን እንገባለን
    ዓመታዊ የስፖርት በዓል
    በወግ ማዕረግ ይከበራል
ወላጆች ተሰብስበው
ዝግጅቱን ኮምኩመው
ውድድሩን አድንቀው
አክሮባቱን ጉድ ብለው
አበራተው ሞራል ሰጥተው
ዕደጉ ተመንደጉ ብለው
    ለስፖርት ትጥቅ መግዣ የሚሆን
    የገንዘብ ድጋፍ ለግሠውን
    ሽልማቱን፣ ዋንጫውን
    በመልክ በመልክ አሸረውን
    ነበር የሚለዩን
    እናት አባቶቻችን
አይ ጊዜ፣ ጊዜ እንዲህ እንደዋዛ
ያንን ሁሉ ውበት፣ ያንን ሁሉ ለዛ
    በጉያው ሸሽጎ
    ድብቅ አርጎ
እያዋዛ እያለሳለሠ
ይዞ እልም አለ፣ ገሠገሠ
    ዳግም ላይመለስ ሄዷል
    ጭልጥ ብሏል፣ ጀንበር ጠልቋል
አቤት ሐኪም ሜዳ ትዝታሽ
አቤት ሐኪም ሜዳ ውበትሽ
አቤት ሐኪም ሜዳ መዓዛሽ
    አሁን እሪ ቢሉ አይመለስ
    የፈሰሰ ውሃ አይታፈስ
ሄዷል ነጉዷል ለዘለዓለም
ብንወድም ብንጠላም።

ቆለኛው
(ሰኔ 2006)

## ዱቤ

ዱቤ ቆፍጣናው
ዱቤ ቀብራራው
ማን ሊደፍርህ ማን ሊነካህ
ከድንጋይ መሃል ጉብ ብለህ ፣ ተሸልመህ
ግርማ ሞገስህ የሚያስፈራ
ዋዛ የማታውቅ ቀብራራ
ድንጋይ መሃል ጉልት ብለህ
አበሻን ታውካለህ፣ ታምሳለህ
የፍርሃት፣ የሃዘን ምንጭ ሆነህ
ህፃኑ ኳሱን ሲያሳድድ፣ ኳሱን ሲከትል
አዋቂው ለሸማው፣ ለጥብቆው ሲሟገት፣ ሲታገል
ሁሉም ጉዳያቸውን ብቻ እያሰቡ
ካንተ ጉያ ካንተ እቅፍ ገቡ
እንደው እንዳመጣላቸው ዘው ብለው
ጥልቅ ብለው ገብተው
ቀሩ ተበልተው
እርጭ፣ ጸጥ ብለው
ዱቤ፣ አንተ እብሪተኛ
አንተ ቀማኛ
እስቲ ለጉዱ ልጠይቅህ
ምንድን ነው ሚስጥርህ?
አቦ ! ዛሬ እንኳን ተናገር
ቀሪው ትውልድም ይመስክር
ከየት አመጣኸው ይህን ጉልበት?
ከየት አገኘኸው ይህን ብልሃት?
አታለኸው፣ አባብለኸው ፣ አማለኸው
ሁሉን ውጠህ፣ ሁሉን ሰልቅጠህ የቀረኸው
አሁን እርቃንህን ቀርተሃል
ቀልብም እርቆሃል
ያ ሁሉ ግርማ ሞገስ ቀርቶ
ውበትህ ረግፎ ተበላሽቶ
ደረትህ ፣ አጥንትህ ገጦ
ጉልበትህ ደክሞ ፣ ጡንቻህ ፈርጦ
ዛሬማ ቀን ጥሎህ ፣ ቀን አዋርዶህ
የህፃናት መጫወቻ ሆነህ ቀረህ
ሲያልቅ አያምር ሆነና ነገሩ፤
ቀርቶ ጉራህ ሁሉ
ያንተ ነገርማ ተረት ተረት፣
ታሪክ ሆኗል አሉ
የት ደረሰ ጉብዝናህ?
የት ገባ ጀግንነትህ?
ወግ አይቀር መቼም
ኩረጃ መማርህ ይሆን አንተም?
ትውልድ ሲደክም ሲኮላሽ
አንተም ያልከው ኩምሽሽ
የሰው ጀግንነት ወንድነቱ
ያገር ፍቅር ጥማቱ
ሁሉም ሲረግፍ ሲጠፋ
ዱቤስ ብቻውን ለምን ይልፋ
ይህን ብለህ ብቻ እንዳይሆን ሰውየው
እንዲህ ቅዝዝ ፣ ድክም ያልከው
እናንተ ከደከማችሁ
ያገር ፍቅር ከጎደላችሁ
የምዬን ጩኸት እየሰማችሁ
ያገሬን ጭንቅ እያያችሁ
ዝም ጭጭ ካላችሁ
እኔስ ማነኝና?
ብለህ ብቻ እንዳይሆን ዱቤ አንበሳው
ጸጥ እረጭ ብለህ የተኛኸው።

ቆለኛው (ሰኔ 2006)

## ለአብሮ አደጎቼ የቀበና - ኮርያ ሰፈር ልጆች

በቀበና ዙርያ የበቀለው ፍሬ
አብቦና አፍርቶ ይህው ታየ ዛሬ
ዘሩንም አባዝቶ በመላው ዓለም
በዚሁ እንዲቀጥል እስከ ዘለዓለም
በቀበና ውሃ ተራጭተን አድገናል
በሀኪም ሜዳ ላይ ኳስ አንከባለናል
በጃንሜዳውም ላይ ፈንድቀን አድገናል
እንቡር ብለናል
ትዝታው አይጠፋም የቀበና ናዳ
ቃኘው በኮርያ የእናታችን ጓዳ
እስቲ እናስታውሳቸው
በሰከነ አእምሮ
እድሜ ተጨምሮ
ያየነው ለዛሬ
የዛሬው ለከርሞ
አሳልፎ ይስጠው
ይንገረው ታሪኩን የቀበናን ፍሬ
አብሮ አደግነቱ አይደለም የወሬ
ይህንን ያሰቡ
ይህንን ያለሙ
ድልድይ ለመዘርጋት
ለአዲሱ ወጣት
ምስጋናዬ ይድረስ እኔም ካለሁበት።

አፈወርቅ መኰንን - ሎንደን
ሰኔ 29 ቀን 2005 ዓ.ም.

## ባለ ዳንቴሏ ሬዲዮ

እሁድ እሁድ የማይቀረው፣ የማይታጎለው
የዘፈን ምርጫው፣ ታላቁ የወቅቱ ሾው
ሐኪም ሜዳ ነበር የሚታየው
ከቀትር በኋላ አስር ሰዓት ሊሞላ ሲል
አንዱ እግዜር የባረከው ብቅ ይላል
ሁሉም በጉጉት የሚጠብቀውን
ባማረ ዳንቴል የተጎናጸፈውን
ያንን የዘመኑን ብርቅዬ እንደ አራስ ልጅ እቅፍ አርጎ
አንዳንዴም ከጉያው ሸሽጎ
ብቅ ይላል እግዜር የባረከው
ያበሻን ልጅ ሊያሸረው
ቀቤን ሊያዝናናው
ሁሉም እርጭ ብለው
በሬዲዮኗ ዙሪያ ተኮልኩለው
ይኮመኩማሉ ተደምመው
ታላቁን የወቅቱን ሾው
የዘፈን ምርጫው ይቀጥላል
እገሊዬ፣ እገሊትዬ ይባባሉልኛል
ሙገሳውም ይቀልጣል
ታዳሚውም ዙርያ ከቦ ይደሰታል
ይዝናናል
አንዷ ላንዱ
ወዳጅ ለዘመዱ
ይሉታል
ይገባበዙታል
አይ ጊዜ አይ ዘመን ፤ አሁን ይህን ማን ያምናል
የባለዳንቴሏ ውለታ እንዲህ ነበር ቢባል
ግና፣ ዳንቴል ለብሳ የተዋበችው
የዘነጠችው
ብርቄ ሬዲዮ ብቻ አይደለችም
ዳንቴሏ ዛሬም አለች አልጠፋችም
በሰለጠነው፣ ባዲሱ ዓለም
ታብሌቱና ላብ ታፑ፣ አይፎኑና አይ ፓዱ
ሁሉም ይጎናጸፋሉ እንዳይቀር ልማዱ
ከብርቄ ሬዲዮ ኮርጀው
የሷን ክብር ተመኝተው
እሁድ እሁድ የማይቀረው፣ የማይታጎለው
የዘፈን ምርጫው፣ ታላቁ የወቅቱ ሾው
የጥንቶቹ የጥዋቶቹ ትዝታና ማዕረግ ነው።

ቆለኛው (ሰኔ 2006)

# ድር ቢያብር

## የልዑል ሣህለ ሥላሴ መታሰቢያ ትምህርት ቤት አመሠራረት

### ከ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. (ትምህርት ቤቱን ለመመሥረት የተቋቋመው ኮሚቴ ካቀረበው ዘገባ በቀጥታ የተወሰደ)


## ክፍል አንድ

ከትምህርት ቤቱ በስተምዕራብ ሲል ከሚገኘው መንደር በሚኖሩ በተወሰኑ ሰዎች ቀደም ብሎ በተጠነሰሰ ቅን ሐሳብ ታህሳስ 29 ቀን 1956 ዓ.ም. አንድ ስብሰባ ተደረገ።

ስብሰባው እንደሀገራችን ባሕልና ልማድ ስለልደቱ በዓል የተሰናዳውን ድግስ ለመመገብ ወይም ለገና ጨዋታ አልነበረም፤ ስብሰባው ይህን ትምህርት ቤት ለመፍጠር የሚያስችል አንድ የኅብረት ችቦ ለማበጀት ነበር። ቀኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ቤዛነት ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዕለት በመሆኑ ሐሳቡ በጥሩ ሁኔታ ተቀናበረ። ከደብዳቤ ጋር ጉዳዩን በቃል ጭምር የሚያስረዳ በሦስት (በ፫) ሰዎች የተወሰነ ቡድን ተመድቦ ቢላክ ይሻላል፤ በማለት ከ፶ አለቃ ጸጋዬ ወልደየስ በቀረበው ሐሳብ መሠረት እራሳቸው የ፶ አለቃ ጸጋዬ የአንዱ ቡድን መሪ ሆነው ሌላውም እንደዚሁ በነመምሬ መኮንንና በነ ፶ አለቃ ገበየሁ ተገኝ ተደልድሎ ለየአካባቢው ዕድር እንዲያስረዳና ሁሉም የሚያገኘውን መልስ ለጥር 6 ቀን 1956 ዓ.ም. እንዲቀርብ ስምምነት ተደረገ። ልዑካኑም ያመጡት መልስ ዓላማው በሙሉ የተደገፈና የተወደደ መሆኑን የሚገልጽ ስለሆነ ጥር 17 ቀን 1956 ዓ.ም. ስብሰባ እንድናደርግ ፕሮግራም ተዘጋጀ፤ ፈቃደኝነታቸውን ላስታወቁትና ለሌሎችም አዲስ ተጋባዦች የጥሪ ደብዳቤ ተላከ፤ ጋባዡና አስተናጋጅ የሆነው (የማኅደረ ሰላም) ዕድር በተወሰነው ቀን ያለውን የዕድር ወንበርና ከየመንደሩም አግዳሚ መቀመጫ በመሰብሰብ ሸክላ ሜዳ ከተባለው ቦታ አሰናድቶ ጠበቀ።

### ከተጠሪዎቹም ውስጥ፡-

| | |
|---|---|
| የማይጨው ጦር | ሰፈር |
| የሊቀመኳስ አጥናፍሰገድ | 〃 |
| የደጃዝማች ገብረስላሴ 1ኛ | 〃 |
| የደጃዝማች ገብረስላሴ 2ኛ | 〃 |
| የደጃዝማች ገድሌ | 〃 |
| የነጋድራስ ጳውሎስ | 〃 |
| የቬላ ሣህለስላሴ | 〃 |
| የወንድማማች | 〃 |
| የሚካኤል ከፋ | 〃 |
| የዕቃ ቤት | 〃 |



በድምሩ ከነጋባዡ የአስራ አንድ ዕድር ሹሞች ከነአባሎቻቸው በተወሰነው ቀን ተገኙ፤ ስለስብሰባው ዓላማም ከጋባዡ ዕድርተኛ አንዱ አቶ ሽብሬ ወ/ማርያም ያዘጋጁትን ጽሑፍ በማንበብ አሰሙ። ሐሳቡ በማናቸውም ኢትዮጵያዊ ልብ ሲጉላላ የቆየና የሚፈለግ ስለነበር የተሰበሰበው ሕዝብ በጋለ ስሜት ተደስቶ ተቀበለው። ቀጥሎም የዚሁ ዕድር ሹም አቶ ንጋቱ ባንቴ፤ የሠፈሩ መምህር አብራራው በመባል የቅጽል ስም የተሰጣቸው አቶ ሀብተጊዮርጊስ ገብረጻድቅና የ፶ አለቃ ጸጋዬ ወልደየስ በየተራ ሰፋ ያለ የቃል ማብራሪያ አሰሙ፤ ተጋባዦቹም አንድ ባንድ እየተነሱ ሐሳቡን በመደገፍ ንግግር ካደረጉ በኋላ ዛሬውኑ ከተሰበሰበው ሕዝብ መካከል ሰው ተመርጦ ኮሚቴ መቋቋም አለበት ተብሎ ስምምነት ተደረገና፣ በሀ እና በ ለ የተከፈለ ኮሚቴ ተቋቋመ።

ሀ- ክፍል የሥራ አስፈጻሚ ሲሆን

ለ- ክፍል ደግሞ በንዑስ ኮሚቴ ደረጃ የተመሠረተ ነበር፤ በዚሁ መሠረት፡-

## በ-ሀ- ክፍል

| | | |
|---|---|---|
| 1. | አቶ ድረስ ወ/ስላሴ | ፕሬዚዳንት |
| 2. | አቶ ንጋቱ ባንቴ | ም/ፕሬዚዳንት |
| 3. | " ሱራፌል ኃይሌ | ም/ፕሬዚዳንት |
| 4. | " ሽብሬ ወ/ማርያም | ዋና ፀሐፊ |
| 5. | " አሰፋ ወ/ጻዲቅ | ም/ጸሐፊ |
| 6. | "ሳህሌ በሻህ | ገንዘብ ያዥ |
| 7. | ሻምበል ታዬ ቁምላቸው | ም/ገንዘብ ያዥ |
| 8. | አቶ ከበደ ካሣ | ዋና ሂሳብ ሹም |
| 9. | ም/፶ አለቃ አበራ ወ/ማርያም | ዋና ተቆጣጣሪ |

## በ-ለ- ክፍል

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ፶ አለቃ ጸጋዬ ወልደየስ | ሊቀመንበር |
| 2. | ሌ.ኮሎኔል አሰፋ ወልደየስ | ም/ሊቀመንበር |
| 3. | የሻምበል ባሻ ዘለቀ ኃይሌ | አባል |
| 4. | አቶ መኩሪያ ጎሹ | " |
| 5. | አቶ ጥላሁን ገብረ ጊዮርጊስ | " |
| 6. | አቶ ጀምበሬ ደስታ | " |
| 7. | የ፶ አለቃ አባተ ተሰፋዬ | " |
| 8. | የ፶ አለቃ ገብረማርያም ጀዌ | " |
| 9. | አቶ ወልደ ሰማዕት ገብረ ጻድቅ | " |
| 10. | የሻምበል ባሻ በትሩ ሀብተማርያም | " |
| 11. | የመቶ አለቃ ጀምበሬ ደለለኝ | " |
| 12. | አቶ ሀብተጊዮርጊስ ገ/ጻድቅ | " |

13. የመቶ አለቃ ብርሃኑ ደጋጋ ጸሐፊ ሆነው ተመረጡ።

ወዲያውም እንደየችሎታው የገንዘብ መዋጮ ማስመዝገብ ቀጥሎ በዕለቱ 550.00/አምስት መቶ ሃምሳ ብር/ ተመዘገበ። የዕለቱ ስብሰባ ይህን ከፈጸመ በኋላ የኮሚቴውን የሥራ መምሪያ ደንብ ዋናው ጸሐፊ አቶ ሽብሬ ወ/ማርያም አርቅቀው ካራት ቀን በኋላ እንዲያቀርቡና በአቶ ንጋቱ ባንቴ መኖሪያ ቤት የምሽት ስብሰባ ተደርጎ ረቂቁ እንዲታረም ወስኖ ስብሰባው ተነሳ።
ወስኖ ስብሰባው ተነሳ።

በተወሰነው ቀን በተመረጠው ኮሚቴ ስብሰባው ቀጥሎ ተዘጋጅቶ የቀረበው ደንብ በንባብ ከተሰማ በኋላ ጥቂት ማሻሻያ ተደርጎበት አዘጋጅውን ዋና ጸሐፊ ኮሚቴው በሰፊው በማመስገን አጸደቀው። ከዚያም የአስተናጋጁ ዕድር አባሎች ያሰናዱት የሻይና የብስኩት ግብዣ ከተደረገ በኋላ ስብሰባው ተነሳ።

በዚሁ ሁኔታ ኮሚቴው በበዓላት ቀን ብቻ ሳይሆን በሥራ ቀኖችም የማታ ስብሰባ እያደረገ ለተነሳበት ዓላማ የሚረዱትን ታላላቅ ሰዎች በሰፊው ካጠና በኋላ፣

ሀ. ክቡር ሌተና ጄኔራል ደበበ ኃይለማርያምን የድርጅቱ የበላይ ጠባቂ፣

ለ. አቶ አበበ ከበደንና አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴን እንደ አንድ አካል በአንድ ሥልጣን የሥራ መሪ ፕሬዚዳንት አድርጎ ሾመ።

የድርጅቱንም መጠሪያ ስም የአካባቢው ሠፈር በሚያጠቃልል ሁኔታ በጃንሆይ ሜዳ፡ በዳግማዊ ምኒልክና በምድር ጦር ሆስፒታል አካባቢ የት/ቤት ሥራ ድርጅት በማለት ሰይሞ በዚሁ ማህተም ተቀረጸ።

ቀጥሎም የአካባቢውን መኳንንትና ወይዛዝርት የክብር አባሎች እንዲሆኑለት ለእያንዳንዳቸው አስታውቆ በዚህ ሁኔታ አቋሙን ካጠነከረ በኋላ ሕዝቡን በየአስፈላጊው ጊዜና ሰዓት እየሰበሰበ ስለትምህርት ቤት መጣበብና በጊዜአችን በመንግሥት ጫንቃ ላይ ብቻ የወደቀውን ሸክም እኛም በመካፈል ገንዘብ እያዋጣን ት/ቤት ሠርተን የልጆቻችን ጊዜ በከንቱ እንዳያልፍ ብናስተምርና ብንረዳዳ ይጠቅማል በማለት አስረዳ። ሕዝቡም ፈቃደኛነቱን ስለገለጸ ለመጀመሪያ መነሻ ከየዕድሩ 15.00/አስራ አምስት ብር/ በማዋጣት ካርኒ አሳትሞ የገንዘብ ስብሰባውን ጀመረ። በዚህም ጊዜ በኮሚቴው ላይ የነበረበት ምን ጊዜም የማይረሳ ስቃዩ የመሰብሰቢያው ቦታ/ማጣቱ/ መከልከሉና በየስብሰባው ቀን አንዳንድ ነገሩ ያልገባቸው ሰዎች ገንዘቡንስ ሰብስባችሁ ለመሆኑ ት/ቤቱን የት ልትሠሩት ነው? ቦታ አግኝታችኋልን? በማለት ለሚቀርብለት ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ነበር። በመጋቢት ፳/፶፺ ዓ.ም ለዚሁ ጥያቄ መፍትሔ ለማግኘት በሥራ መሪዎቹ ፕሬዚዳንቶች ሰብሳቢነት የክብር አባሎችን ጋብዞ ስለገንዘብ ሳይሆን በቦታ በኩል ለሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ካቅሙ በላይ ሆኖበታልና በእናንተ በኩል ለመረዳት እንፈልጋለን በማለት ራፖር አቀረበ። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ያን የተፈራ ጥያቄ በማስቀደም እንዲያውስ እናንተ እነማናችሁ? ቦታስ ሳታገኙ ገንዘብ መሰብሰብ ለምን ጀመራችሁ? በማለት ጅምራችንን በመንቀፍ የተግሳጽ ቃል ሰነዘሩ። ሌላውም ሁለተኛ ሰው የተናጋሪውን ሰው ሐሳብ እደግፋለሁ አሉ። በዚህ ጊዜ በኮሚቴው ኃላፊዎች ላይ ደረሰውን ድንጋጤ ለመግለጽ ቃላት አይገኙም። በሰማይ ነፍሳቸውን ይማረውና ሟቹ የተከበሩ ቀኛዝማች ተፈሪ መንገሻ፡ አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴና አቶ ተፈራ ተድላ ከፈተው አቶ መክብብ መኮንን በየተራ እየተነሱ እነኚህ ሰዎች እኮ የተነሱበት ዓላማ በጣም የሚደገፍ ነው አቅማቸው

በሚችለው መጠን ድርጅቱን አቋቁመው በቂ ገንዘብ ሰብስበዋል። በቦታው ማግኘት በኩል ከእኛ እናንተ ትሻላላችሁ በማለት በዛሬው ቀን እንድንሰበሰብ አድርገው ይህንኑ ችግራቸውን በራፖራቸው ገልጸዋል።

ስለዚህ እነሱ እንዳሉት ሁሉ የቦታውን ማፈላለግ ኃላፊነት ልንረዳቸው ስለሚገባን አቀራረባቸው ትክክለኛና የሚገባ ስለሆነ በዚህ ነገር መርዳት የሚገባን ሰዎች አሁኑኑ ተመርጠን በሚያስፈልገው መንገድ እንከታተል። እነርሱ ግን ገንዘቡን ከመሰብሰብ ማቋረጥ የለባቸውም፤ እኛንም እያስታወሱን፤ በማለት ለሐሳባችን ተቃዋሚዎች መልስ ከሰጡ በኋላ ለዚሁ ሥራ ክብር አቶ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ አማኑኤል፥ አቶ አበበ ከበደና አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ ተመርጠው ኃላፊነቱን ስለወሰዱ በድንጋጤ የተረበሸው ኮሚቴ ለጊዜው የደስታ መንፈስ ለበሰ።

ደፋርና ጨስ መውጫ አያጣም እንደተባለው የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በገንዘብ አሰባሰብና በቦታው አፈላለግ በኩል የገባበትን ግዴታ ከግቡ ለማድረስ ጥረቱን እንደቀጠለ በአቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ የአልተቆጠበ ድካምና በክቡር ቢተወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት፤ ያን ጊዜ ከንቲባ ረዳትነት የነበሩ፤ መጋቢት ፳፯/፲፱፻፶፯ ዓ.ም. ለዚያ ቦታ አላችሁ ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልስ በማግኘት የተስፋ ቃል አሰሙ። ተስፋውም ተስፋ ብቻ ሆኖ አልቀረም፤ ይህ ት/ቤቱ የተሠራበት ቦታ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድ ለድርጅቱ የት/ቤቱ መሥሪያ በግንቦት ወር ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. ተሰጥቶት ተረከበ።

ኮሚቴው ትምህርት ቤቱን የት ልትሠሩት ነው ገንዘብ የምትጠይቁን? ለሚለው የሕዝብ ጥያቄ መልስ በማግኘቱ ቢደሰትም ባንድ ወገን ደግሞ ካለፈው የጥረት ዘመኑ የባሰና የማይወጣ ገደል የሆነ ችግር ገጥሞት ነበር።

## ይኸውም

1ኛ. ሕዝቡን በየጊዜው በስብሰባ ከአንድ ዓመት በላይ ስላሰለቸውና በዚህም ጊዜ የተሰበሰበው ገንዘብ ከ5000.00/አምስት ሺህ ብር/ ያልበለጠ ስለነበር ሥራውን በምን መጠን ለመጀመር ማወቅ ባለመቻሉ።

2ኛ. ተከታዩም ጊዜ ክረምት በመሆኑ በዚያ ወራት ሕዝቡ ከራሱ ችግር ተርፎት ገንዘብ ሊያወጣ ባለመቻሉ።

3ኛ. ተሰብስቧል በተባለው ገንዘብ ሥራው ካልተጀመረ ደግሞ ለወደፊቱም ሕዝቡ በኮሚቴው ላይ እምነት ኖሮት ሌላ ገንዘብ ሊያወጣ ካለመቻሉም ሌላ በሥራው መዘግየት በመንግሥትም በኩል ግምት ይወስድብኛል በማለት፤ በጠቅላላው ይህንንና ይህን የመሳሰሉት እንቆቅልሾች ነበሩ የገጠሙት።

ኮሚቴው ይህንኑ ችግሩን ግምባር ለግምባር በመጋጠም በክቡር ሌ.ጀኔራል ደበበ ኃ.ማርያም ፈቃድ ከክብር ዘበኛ መ/ቤት በትውስት በተፈቀደለት ግሬደር ቦታውን ሲየስደለድልና ሕዝቡንም በየእድሩ ስብሰባ ላይ በመገኘት የመዋጮው ክፍያ እንዳይቋረጥበት በምክር ሲያበረታታ ክረምቱን አሳለፈ። መስከረም እንደ ጠባም ቤቱ በግምብ ይሠራ ወይስ በጭቃ ይሠራ በማለት በኮሚቴውም መካከል ያለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። በጭቃ ይሠራ ያለው ወገን በድምጽ ቢያሸንፍም በግምብ ይሁን ያለው ወገን በመሐንዲስ ስለተደገፈ በግምቡ ሥራ መሠረቱ በጥቅምት ወር 58 ዓ.ም ተጀመረ። የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትም ፕላኑን በነፃ ሠርቶ ከመስጠቱም በላይ ሚስተር ኤቫን የተባሉ የክፍሉ መሀንዲስ ሥራውን እንዲቆጣጠሩ በመፍቀዱ ድርጅቱን በሚገባ ረድቷል።

ከዚህም በላይ በቤቱ ሥራ መጀመር ሕዝቡ በመደሰት ሐሳቡን ከወጠነው 11 ዕድሮች በዓላማው በገፉት ስምንት እድሮች ጥረት ከየዕድሩ ካፒታልና የየግል መዋጮውም በመጣደፍ ተሰበሰበ። የቀን ሠራተኛውም ሳይቀር በጉልበቱ ለመርዳት በፈቃደኝነት እየቀረበ ለኮሚቴው ቃል ገባ። እንዲሁም የማይረሳው ቁምነገር ጥቅምት 7/1958 ዓ.ም. በነበረው ጠቅላላ ስብሰባ ቀን ከ10 ዓመት በታች እድሜ ያላቸው ሕጻናቶች በበኩላቸው ከ5 ሳንቲም እስከ 1.00 /አንድ ብር/ ድረስ ከየወላጆቻቸው በመለመን ባደረጉት መዋጮ በድምሩ 9.50/ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሣንቲም/ ለድርጅቱ ማበርከታቸው ነበር። ይህን ምሳሌ የጠቀስነው ገንዘቡ ከፍተኛ ነው ለማለት ሳይሆን ለኅብረት ዓላማ ሕፃናቶች እንኳ እንደሚተባበሩ ለመግለጽ ያህል ነው። በተጠቀሰው ቀን በጥሬ ገንዘብና በልዩ ልዩ ዕቃዎች ርዳታ የተገኘው ገቢ ከ2500.00 ብር በላይ ነበር። ኮሚቴው በፕላኑ መሠረት ለሕንፃው ሥራ የሚበቃ የተጠቃለለ ገንዘብ ባለማግኘቱ ሕንፃውን ያሠራው በኮንትራት በሥራ ተቋራጭ ሳይሆን በራሱ ተቆጣጣሪነት በየሥራው መልክ በካሬ ሜትር ራሱ እየተዋዋለ ነበር። ሕዝቡ ድንጋይ በማጋዝና በልዩ ልዩ ሙያው በመረዳዳት ሲሆን የቤቱም ዕድል እያማረና እያደገ በመሔዱ ከግርማዊ ን.ነ. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የ5000.00/አምስት ሺህ ብር/ እርዳታ ተሰጠው። ወዲያው ልዕልት ሂሩት ደስታ 500.00/አምስት መቶ ብር/ ሰጡ። ክቡር ሌ/ጀኔራል ደበበ ኃይለማርያም ከግል ገንዘባቸው 300.00/ሦስት መቶ ብር/ በመስጠት የክብር ዘበኛ ሙዚቃ ተጫዋቾች የጨዋታ በዓል አሳይተው የገንዘብ ገቢ እንዲስገኙልን በሰጡት ትእዛዝ መሠረት 1529.00/አንድ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር/ ተገኝቷል። ቀጥሎም ክቡር አቶ ዓለመ ሥላሴ፤ አቶ አበበ ከበደ፤ አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ በሰጡት ጥሬ ገንዘብና የሥራ ተካፋይነት የቤቱ ሥራ በመካሔድ ላይ እንዳለ፤ በአቶ አበበ ከበደ አማካይነት ከአሜሪካን ተራድኦ የ11,452.50/አስራአንድ ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር ከ ሃምሳ ሳንቲም እና ልዩ ልዩ እቃዎች ጭምር ሊገኙ ችለዋል።

አቶ ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ ደግሞ ለሕንፃው የሚበቃ መስኮትና ልዩ ልዩ ዕቃዎች በቀላል ዋጋ ከማስገኘታቸውም በላይ ለክፍሎቹ ወለል የሚበቃ የሸክላ ንጣፍ በግል ገንዘባቸው ገዝተው አበርክተዋል፤ አቶ ተፈራ ተድላ ክፈተውም ለቤቱ ሥራ የሚበቃውን ያህል የባህር ዛፍ አጠና በችሮታ ሰጥተዋል። ቀጥሎም ክቡር ኮሎኔል ዘውዴ ኃይለማርያም፤ ክቡር አፈ ንጉሥ ኃይሌ ወልደ ኪዳን፤ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ጠብቄ፤ ክብርት ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ ኃይለ ማርያምና በሌሎችም በጎ አድራጊዎች የገንዘብና የሐሳብ ድጋፍ ትምህርት ቤቱ ከሞላ ጎደል ለአገልግሎት ስለደረሰ መስከረም 19 ቀን 1959 ዓ.ም. በግርማዊ ን.ነ. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተኅብኝቶ በዚሁ ዘመን 500 ለሆኑ ህጻናት ትምህርት መስጠት ጀመረ። የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ሕዝቡን ለኅብረቱ ሥራ እንዲተባበር ልዩ ልዩ የኅብረት ሥራ ውጤት ፊልሞችን በማሳየትና በድምጽ ማጉያ መሣሪያ በየስብሰባው ቀን ከነሠራተኞቹ አቅርቦ

በሚገባ ረድቷል። እንዲሁም የክብር ዘበኛ መሐንዲስ አዛዥ ኰ/ል በቀለ ግዛው የዚሁ ክፍል ተጫዋቾች፤ ሾፌሮች በተለይም የ፻ አለቃ ቸርነት ጅማ፣ አቶ ብዙነህ እንደሻውና የ፶ አለቃ ገበየሁ ተገኝ በሚቻላቸው ሁሉ በቴክኒክ ችሎታቸው ድርጅቱን አገልግለዋል።

# ክፍል ሁለት

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ የመጀመሪያውን ኮሚቴ ለውጦ ሌላ ኮሚቴ ማቋቋም ስለፈለገ ኮሎኔል ጌታቸው ፍላቴ አስቀድሞም የኮሚቴው የክብር አባል በመሆን በገንዘብና በሐሳብ ድርጅቱን ከልብ በማገልገላቸው ኮሚቴው ለሥራው መሪነት አስፈላጊ መሆናቸውን ስላመነበት ባንድ ድምጽ ለፕሬዚዳንትነት ሊመርጣቸው ቻለ፤ መራጩ ኮሚቴ ከነባሮቹ ሹማምንቶችና አባሎችም ውስጥ እምነታቸውን ያላጓደሉትንና ለሥራው ተፈላጊ የሆኑትን በየነበሩበት ሥራ እንዲቀጥሉ እንደገና በመምረጥ አዲስ ኮሚቴ መሠረተ፤ ይህም የተደረገው ምርጫ እንደቀድሞው ጊዜ አንዱ ስለሌላው ታሪክ ሳያውቅና ሳያጠና በድንገት የተፈጸመ ሳይሆን በሥራው ላይ አብሮ በመቆየት ብስልና ጥሬውን በመለየት በጥንቃቄ የተፈጸመ ምርጫ ስለነበር ስለገንዘብ አሰባሰብ፤ ስለአያያዙና ስለአወጣጡም ምንም ችግር ያልደረሰበት ከመሆኑም በላይ በተለይ በሥራው አመራር በኩል ፕሬዚዳንቱ ባላቸው የረጅም ዘመን የሥራ ልምድ ባለማወቅ የሚባክነውን ጊዜና ገንዘብ ከማስቀረቱም በላይ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ዕቃዎች ማቅረቢያ መኪና በነፃ በመስጠት የድርጅቱን የወጪ በር በማጥበብ ከልብ ረድተዋል፤ በዚህም በአዲሱ ምርጫ ለሥራ አስፈጻሚው ክፍል የተመረጡት፤

1. ኮሎኔል ጌታቸው ፍላቴ ............ ፕሬዚዳንት
2. የሻምበል ባሻ በትሩ ............. ም/ፕሬዚዳንት
3. አቶ ሣህሉ ሰይፉ ............... ም/ፕሬዚዳንት
4. አቶ ሽብሬ ወ/ማርያም .......... ዋና ጸሐፊ
5. አቶ ወርቁ ከበደ ............... ም/ጸሐፊ
6. አቶ ከበደ ካሣ ................ ዋና ሂሳብ ሹም
7. አቶ ተፈራ ደምሴ" ............. ተቆጣጣሪ
8. አቶ ሣህሌ በሻህ ............... ገንዘብ ያዥ

ለንዑስ ኮሚቴው ክፍል

1. የሻምበል መስቀሉ ዋቀየ ........... ሊቀመንበር
2. ባሻ ገሠሠ ገልምጤ ............ ም/ሊቀመንበር
3. አቶ አሰፋ ወ/ጻድቅ ............. ጸሐፊ
4. የሻምበል ባሻ ዘለቀ ኃይሌ ......... አባል
5. የ፶ አለቃ አስረስ ኃ/ጊዮርጊስ ....... "
6. አቶ ብርሃኑ ወ/ሚካኤል ......... "
7. የ፶ አለቃ ቸርነት ሳንድሮስ ......... "
8. አቶ መላኩ መሰለ ............. "
9. የ፶ አለቃ ዓለሙ ገብርዬ .......... "
10. የም/፻ አለቃ ወ/አማኑኤል ወ/እየሱስ. "
11. አቶ ገድቤ ፋንታዬ ........... "
12. አቶ ገብረሚካኤል ማሞ .......... "
13. አቶ ለገሠ ወ/ሰማዕት .......... "
14. የ፶ አለቃ ሙሉጌታ ገ/መስቀል ..... "
15. የ፲ አለቃ ገብረጊዮርጊስ ቱፎ ...... "
16. ባላንባራስ ጥላሁን ወ/ማርያም ..... "
17. የ፶ አለቃ ተፈራ ኃይሌ ......... "
18. የ፶ አለቃ ገብሬ ወ/ማርያም ...... "
19. የ፶ አለቃ ዜና መንገሻ .......... "
20. የ፶ አለቃ ታፈሰ ወንድም አገኘሁ .... "
21. የ፶ አለቃከበደ ጌጤ ........... "
22. አቶ ጥላሁን ገ/ጊዮርጊስ ........ "
23. አቶ ዘውዴ ተገኝ............. "
24. ም/፶ አለቃ ስለሺ ሀብተየስ ....... "
25. አቶ ከበደ ጣሴ ............. "
26. አቶ ከበደ በሻህ ............. "
28. አቶ መንግሥቴ ............. " ናቸው።


ነገር ግን ከአባሎቹ ውስጥ ለተወሰነ ዘመን እየሠሩ በመተው በለውጥ እየገቡ ሌሎች ሰዎች ሠርተዋል። በዚህ አኳኋን ተመሥርቶ የተቋቋመው ኮሚቴ ሥራውን በአዲስ መንፈስና እቅድ ቀጥሎ ባጭር ጊዜ ከ17000.00/አስራ ሰባት ሺህ ብር/ በላይ ከሰበሰበ በኋላ በ1961 ዓ.ም ለወደፊቱ ከፍተኛ ህንፃ እስኪያሠራ ድረስ በ2837.00/ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ ሠባት ብር/ ስድስት ክፍሎች ያሉት ጊዜአዊ የቆርቆሮ ግድግዳ ቤት ሠርቶ ከ200 ያላነሱ ልጆች ትምህርት እንዲገበዩበት አደረገ። ከዚህም በቀር ወደፊት ሕንፃው የሚሠራበት ቦታ ዳገትና ገደላገደል ስለነበር በትራክተር እያስቆፈረ በማስደልደል ለነዳጅ፣ ለሾፌሮች የውሎ አበል ለቀድሞው ቤት የውስጥ ሥራ ማጠናቀቂያ ወጪ አድርጎ ካሠራ በኋላ ለዋናው ሕንፃ ማሠሪያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሟላት በአንዳንድ ለድርጅቱ ዓላማ ቅን ሐሳብና ፈቃደኝነት ባላቸው አባሎች በቀረበው ሐሳብ መሠረት ለብሔራዊ ሎተሪ አድሚኒስትሬሽን የገንዘብ ልመና ጥያቄ ቀርቦ የ8000.00/ስምንት ሺህ ብር/እርዳታ ተገኘ። በዚያውም ጊዜ የስዊድን ተራድኦ ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ግማሽ ገንዘብ እየሰጠ ት/ቤት መሥራት ስለጀመረ ይህም ድርጅት የሰበሰበውን 23697.00/ሃያ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ብር/ ከበጎ አድራጊው ድርጅት ጋር በማዋጣት በጠቅላላው በ47394.00 /አርባ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና አራት ብር/ አስር የመማሪያና አሥር የመጸዳጃ ክፍሎች ያሉት ህንፃ አሠርቶ በ1962 ዓ.ም. 465 ተማሪዎች ተቀብሎ ለማስተማር ችሏል። እንዲሁም በዚሁ ዘመን የቀድሞውን ሕንፃ ጠቅላላ እደሳ ከማድረጉም በላይ ከዋናው አስፋልት ጎዳና እስከ ት/ቤቱ ድረስ ያለውን መንገድ በሚገባ አሠርቶ በሥራ ላይ አውሏል። ይህንንም የመንገድ ሥራ ከግቡ ሊያደርስ የቻለው ከፖሊስ ሠራዊት የድንጋይ ማቅረቢያ መኪና፤ ከክብር ዘበኛ ሩሎ ነዳጅና የሹፌሮች አበል ችሎ በትውስት በማግኘቱ ስለሆነ እነዚህ ድርጅቶች ለዚህ ት/ቤት ውለተኞች መሆናቸውን ኮሚቴአችን ከምስጋና ጋር ያረጋግጣል።

በያዝነው በ1963 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በለቀቁትና በሌሎችም ሥራ ሳይዙ በከረሙት ክፍሎች ከ355 ያላነሱ ልጆች ወደ ትምህርት ገበታ ጋብዟል። ይህ ት/ቤት በሰፈሩ ሕዝብ አማካይ በሆነ ቦታ ላይ የተሠራ በመሆኑ ከቀን ተማሪዎች ሌላ ከ300 የማያንሱ የማታ ተማሪዎች ዕውቀት

የሚገበዩበት ሲሆን ድርጅቱ አንዳችም ሂሳብ አያስከፍልም። ኮሚቴው በወላጆች ላይ የጣለው ግዴታ በአንድ ልጅ 20.00/ሃያ ብር/ ብቻ ሲሆን ይህንንም መክፈል የማይችሉ የድሆችና የሙት ልጆች የሆኑ 66 ልጆች በነፃ አስገብቶ ያስተምራል። የድርጅቱን የመጀመሪያ ዓላማ በመናቅ በዚሁ ሠፈር ውስጥ ተቀምጠው የገንዘብ ክፍያ ሳይጀምሩ የቆዩትን ግን ኮሚቴው በቅጣት መልክ ከሌላው 10.00/አስር ብር/ በመጨመር በአንድ ልጅ 30.00/ሰላሣ ብር/ ያስከፍላል። እስካሁን በዚህ ት/ቤት በቀን የሚማሩት ብቻ ከ1520 በላይ ናቸው፤ አሁን ከመስከረም 17 ቀን 1963 ዓ.ም ጀምሮ የብሔራዊ አንድነት መረዳጃ ማኅበር በመባል የታወቀው ዕድር አዲስ ስለገባ ድርጅቱ 9 ዕድሮች የሚያጠቃልል ነው።

ት/ቤቱ እስካሁን ባካባቢው ሠፈር ስም ሲጠራ ቆይቶ አሁን ዕድገቱ እያማረና እየተስፋፋ በመሄዱ ለዓላማው ተስማሚ ስም እንዲኖረው፤ አስፈላጊነቱን ኮሚቴው ስላመነበትና ሠፈሩም ቪላ ሣህለ ሥላሴ በመባል የሚጠራ ስለሆነ ይህ ት/ቤት የልዑል ሣህለ ሥላሴ መታሰቢያ ትምህርት ቤት በመባል እንዲሰየምለት ኮሚቴው ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለስላሤ ባቀረበው ልመና መሠረት ስለ ተፈቀደለት ት/ቤቱን ለሁለተኛ ጊዜ በመምጣት በዛሬው ቀን መርቀው ስሙንም በልዑልነታቸው ስም ስለሰየሙት እነሆ ከዛሬ ከጥቅምት 9 ቀን 1963 ዓ.ም. ጀምሮ የልዑል ሣህለሥላሴ መታሰቢያ ትምህርት ቤት ተብሎ ተሰየመ፤ ከእንግዲህ ወዲያ የዚህ ት/ቤት ደረጃ በቅርቡ ጊዜ በጣም ከፍተኛ እንደሚሆን በዚሁ ለመረዳት ይቻላል። ይህ ት/ቤት ባጭር ጊዜ ውስጥ እስከዚህ ሊደርስ የቻለው በተባበሩት ስምንት ዕድሮች ጠንካራነትና፤ በጠቅላላው የሕዝቡ ተባባሪነት ከየዕድር ካፒታላቸው 14770/ አስራ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ብር/ ከማውጣታቸውም በላይ ሕዝቡም የነፍስ ወከፍ ክፍያውን ከሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በሚሰጣቸው መመሪያ መሠረት በማስከፈላቸውና በጉልበትም ጭምር በመሥራታቸው ነው።

በተለይም የኮሚቴው ዋና ጸሐፊ፤ ገንዘብ ያዢውና ሂሣብ ሹሙ ባላቸው የሥራ ችሎታና ታማኝነት ከልብ በመነጨ ፍላጎት ይህን ድርጅት እዚህ ለማድረስ የፈጸሙት አገልግሎት ለሠፈሩ ሕዝብ ምን ጊዜም የማይረሱ ውለተኞች መሆናቸውን ኮሚቴው አረጋግጦላቸዋል። ይህ መጽሐፍ ለነርሱና በጠቅላላ በየችሎታቸው ይህን ድርጅት ለረዱት ሁሉ ምስክር ሆኖ ለተከታይ ትውልድ እንዲተላለፍ በት/ቤቱ ጽ/ቤት ለዘላለም በክብር ይቀመጣል። ድርጅቱ ሥራውን በዚህ የማያቆም እንደመሆኑ መጠን ወደፊትም የሚሠራውን ሁሉ በመጽሔት የሚገልጥ ቢሆንም ካሁን በፊት ለተሠራው ሥራ እንደየችሎታቸውና ፍላጎታቸው በጥሬ ገንዘብም ሆነ በልዩ ልዩ ዕቃና በጉልበትም፤ በዕውቀታቸውም የረዱት ውለተኞች ስም ዝርዝር ከዚህ መጽሐፍ ጋር ተያይዞ እንዲቆይ መዝገቦ አኑሮታል።



# የፎቶ አምድ



የመጀመሪያውን የቀበና ኮርያ ሠፈር የአብሮ አደጎችና የቤተሰቦቻቸው መሰባሰቢያ ቀን ዝግጅትን ካስተባበሩት መካከል፤ ጁላይ 5 ቀን 2013







ሁለት ቀቤዎች ፣ የትናንት አፍሮዎች ፣ የዛሬ ...



በመጀመሪያው የቀበና ኮርያ ሠፈር የአብሮ አደጎችና የቤተሰቦቻቸው መሰባሰቢያ ቀን ላይ ከተገኙት መካከል የቀድሞ ትዝታቸውን ሲኮመኩሙ፤ ጁላይ 6 ቀን 2013



አንድ ቤተሰብ





አብሮ አደጎች




በኮርያ ዋና ከተማ በሶል ከተማ በሚገኘው የኮርያ የጦርነት መታሰቢያ ሙዚየም (War Memorial) ውስጥ የሚታዩ በኮርያ ጦርነት የተሳተፉት የኢትዮጵያ ሰራዊት አባላት ለብሰዋቸው የነበሩ ወታደራዊ መለዮዎች (ፎቶ፤ ወርቁ ዳመና)



የቀድሞው ክብር ዘበኛ በሰልፍ ትርዒት ላይ



ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል



ቀበና፤ ዱቤ ባህር











ቤት ለምቦሳ ... እምቦሳ እሰሩ።



አንድ ቤተሰብ





# ለምርጥ ስጋና የተለያዩ የኢትዮጵያ ምርት ውጤቶች፤ ሰላም ገበያን ይጎብኙ



ክትፎ
ጥሬ ስጋ
ዝልዝል ጥብስ
ጎድን ጥብስ
ቋንጣ

እንጀራ
ጤፍ ዱቄት
ኦርጋኒክ ገብስ ዱቄት
ኦርጋኒክ አጃ ዱቄት
የማሽላ ዱቄት

የኢትዮጵያ ቡና
የቡና ጀበና እና ሲኒ
ቅመማ ቅመማት
ምጣድ
ባህላዊ የኤሌክትሪክ ምድጃ

## ገንዘብ ባፋጣኝ ወደ ኢትዮጵያበተመጣጣኝ ዋጋ እንልካለን!!

5012 N. Sheridan Rd., Chicago, IL 60640
Store #: (773) 271-4300 • Fax#: (872) 203-9144
Cell#: (773) 879-1305 • www.yelp.com/biz/selam-market-chicago

በሰሜን አሜሪካ ምርጥ እንጀራ እያቀረብን መልካም አስተያየትዎን በሚከተለው ድረ ገጽ እንዲገልጹልን እንጋብዛለን

**www.yelp.com/biz/selam-market-chicago**

